# ማዕዶት



ሚያዝያ ፲፱፻፹፫ ዓ/ም

ቁጥር ፴፱

አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

የግል ቤተ መጻሕፍት

# ማዕዶት

ሚያዝያ ፲፱፻፹፫ ዓ/ም
ቊጥር ፴፱
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

## ማ ዕ ዶ ት

ማዕዶት የሚለው ቃል መሠረታዊ አመጣጡ ከልሳነ ግእዝ ሲሆን ትርጓሜውም መሸጋገሪያ (ድልድይ) ማለት ነው ። ይህ መጽሔት በተሐድሶና በዕድገት ላይ የምትገኘውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን እምነትዋንና ሥርዓቷን ፣ ወቅታዊ እንቅስቃሴዋን ልዕልናዋንና ዜናዋን ሁሉ የሚገልጽ ስለሆነ ማዕዶት ተብሎ ተሰየመ

መጽሔቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወሩ አንድ ጊዜ እየታተመ ይወጣል ።

ዋና አዘጋጅ

ሊቀ ትጉሃን ገ/ክርስቶስ ኃ/ማርያም

አ/አበባ ሚያዝያ ፲፱፻፹፫ ዓ/ም ስልክ ቍ 11 26 63

## ማ ው ጫ


| ተራ ቍ. | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | ርእስ አንቀጽ | ፭ |
| ፪ | የቅዱስ ፓትርያርክ ቃለ ምዕዳን | ፱ |
| ፫ | ትዳሜ ሥዐር | ፲ |
| ፬ | የተፈጥሮ ፀጋ | ፲፪ |
| ፭ | እናትህ እኅኣት | ፲፬ |
| ፮ | ቅዱስ ጊዮርጊስ | ፲፮ |
| ፯ | ዋና ሥራ አስኪያጁ | ፲፰ |
| ፰ | የሃይማኖት ብዛት | ፳ |
| ፱ | የመምህር እሸቱ | ፳፩ |
| ፲ | የጤና አምባ እድር | ፳፪ |
| ፲፩ | ክርስቲያናዊ ሕይወት | ፳፬ |
| ፲፪ | አስደናቂ ተአምር | ፳፮ |
| ፲፫ | የሰንበት ት/ቤት | ፴ |




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

አድት ረታና ቤተሰብ ... የግል ቤተ መዛግብት

# በኵረ ትንሣኤ

ብኵርና በድሮ ዘመን እጅግ ትልቅ ክብር ያለው ነው በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ የ ሚጠቀሰው ስለወንዶች ብኵርና ነው አባት በሌለበት ቤት ሥልጣኑለበኵር ልጁይሰጥና የወንድሞቹን ሁሉ ኃላፊ ሆኖእንዲያስተዳድርያደርጋል፡፡በመጽሐፍቅዱስእንደምንመለከተው(በቤተእስራኤል)በያዕቆብ ቤት ያዕቆብበሌለበትጊዜየበኵርልጁሮቤል የወንድ ሞቹንኃላፊ ሆኖ ይመራ ነበር ፡፡ እንዲሁም ክርስት ሁለት እጅ ያገኝ እንደነበረ እንረዳለን ፡፡ በቤተ መንግሥትም ቢሆን አልጋ ወራሽ የሚሆነው የመጀመሪያው ወይም የበኵር ልጅ እንደሆነ በጥንትም ባሁኑም የሚታይና የሚታወቅ ነው ፡፡

በሀገራችን በኢትዮጵያም እንደዚሁ ነው ታላቁ እያለ ታናሹ አባት በሌለበት በቤቱ አይሰለጥንም ይልቁንም በሰሜን ክፍላተ ሀገራት ይህ ባሕል (ሥርዓት) እስካሁን ድረስ በጥብቅ ይሠራበታል ታላቁ (በኵሩ) ከእርሱ በታች ያሉትን ወንድሞችና እኅቶች በስነ ሥርዓት ይቀጣል ያዛል ፡ ይልካል ያሠራል ያስተናብራልከሌላከውጭእንድጉዳይደዞየመጣሰውባለቤቱ እንደሌለ ከተረዳ ታላቁን (የበኵር ልጁን) ጠርቶ ያነጋግራል ፡ ሊሆን የሚገባ አስቸኳይ ጉዳይ ካለም የሚፈጸምበትን መንገድ እንዲቀይስ የማጠናከሪያ ሀሳብ ሰጥቶት ይሄዳል ፡፡

ስለበኵር ብዙ ማስረጃ ለማቅረብ ቢቻልም በመጠኑም ቢሆን ከዚህ በላይ ያተትነው ይብቃንና ወደተነሣንበት ዋና ዓላማ እንመለስ የበኵር መብትና ሥርዓት ካተትን ዘንዳ በርእሱ መሠረት «በኵረ ትንሣኤ» ማለት የትንሣኤ በኵር የተባለው ማነው ? ወደሚለው ጥያቄ ብናዘነብል መልካም ነው መቼም ሁላችን እንደምናውቀው ተወልደን አድገን ለቁም ነበር እስከ በቃንበት ጊዜ ድረስ ሙቶ ተቀብሮ እስከ ሦስት ቀን ከቆየ በኋላ ሞትን ድል ነሥቶ የተነሣ አንድ ብቻ ነው እርሱም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፡፡

ሞትን ያህል ክፉ (ጨካኝ) ነገር አሸንፎ የመነሣት ሥልጣን ያለው ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቈጠረ አንድም ፍጡር አይገኝም ሁሉን የሚችል ሞትን የመግዛት ሥልጣን ያለው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ለኛ ለተከታዮቹ ኃያልነቱን ፡ ሁሉን ቻይነቱንና አሸናፊነቱን አርአያና ተስፋ ይሆነን ዘንድ ሙቶ በሦስተኛው ቀን መቃብር ከፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሣይል ከመቃብር አፈፍ ብሎ ተነሣ፤መቃብሩን አጽንተው ይጠብቁት የነበሩት ጽኑዓን የሮማ ወታደሮችም ዓይናቻቸው በብርሃን መለኮቱ እስኪደመሰሱ ድረስ ሆነዋል ፡፡ የሚይዙት የሚጨብጡትና የሚናገሩትም አጥተው ከመደናበራቸውም በላይ የኋሊት ተንጋለው ወድቀዋል ፡፡

ከዚያች ሰዓት ከዚያች ሌሊት ጀምሮ መድኃኒታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰዎችን (የሙታንን) ሁሉ በኵረ ትንሣኤ እየተባለ ሲጠራ ይኖራል አዎን በዚህም ላይ ሁለት ዓይነት ትንሣኤ እንዳለ ለመገንዘብ እንድንችል አድርጎናል በወንጌሉም አስተምሮናል ፡፡

ይኸውም ሁለት ዓይነት ሞት የተባለው ሞተ ነፍስ ፡ ሕይወተ ነፍስ መኖሩንና ይህም የሚገለጽበት ወቅት እንዳለ ማወቅና መረዳት ነው ፡፡ ይህም ማለት ሀልዎቱን የሚክዱ ፡ ትእዛዙን የማይፈጽሙና ሕጉን የማያከብሩ ሥጋንም ነፍስንም አጥሕዶብዝኂንም ያቀጣቸዋም ሀልዎቱን በንጹሕ አምልኮት የሚፈጽሙ ትእዛዙን ሕጉን የሚያከብሩ ደግሞ ሥጋና ነፍስን አዋሕዶ ዓለም ሳይፈጠር ባዘጋጀው በክበረ ቦታ በመንግሥተ ሰማያት ለዘለዓለም በሕይወት ያኖራቸዋል ፡፡ ለነዚህም ሁሉ ብርሃን ተጎናጽፎ የጽልመተ ዲያብሎስን ኃይል አሸንፎ በኵረ ትንሣኤውን አሳይቶአቸዋል ፡፡ ስለዚህም ክርስቲያኖች ሁሉ ቅዱስ ጳውሎስ ለሰብአ ቆላስይስ በጻፈው መልእክቱ «እርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው ፤ እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ መጀመሪያ ከሙታንም በኵር ነው » ብሎ የጻፈላቸው ቃሉ ሁል ጊዜ ከፊታቸው እንደተሣለ ሆኖ ይኖራል እንጂ አይጠፋም ፡፡ ሞቱን ትንሣኤውን አምነን በሕገ ጸንተን ለምንጠብቀው ሁሉም እንደዚሁ ነው ፡፡

ወንጌላዊው ዮሐንስም ይህንኑ በማገናዘብ ለመሰሎቹ ክርስቲያኖች ሰላም እንዲሆንላቸውና እንዲበዛላቸው በመመኘት ሲጽፍ «ካለውና ከነበረው ከሚመጣውም በዙፋኑም ፊት ካሉት ከሰባቱ መናፍስት ፣ ከታመነውም ምስክር ፣ ከሙታንም በኵር የምድር ነገሥታት ገዥ ከሆነ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን» ብሎ በእስያ ለነበሩና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስለታመኑ የትንሣኤብርሃንን ይጅ ለሚጸኑ ክርስቲያኖች ከዚህ በላይ የተመለከተውን ይጽፍላቸዋል ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዘረ ትንሣኤነት እንደ እንግዳ ደራሽ እንደውኃ ፈሳሽ ሳይሆን አስቀድሞ ሐዋርያት በሦስት ነገሮች አረጋግጠዋል ። እነርሱም በብሉይ ኪዳን ቅዱስ ዳዊት «ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና ቅዱስህንም መስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም የሕይወትን መንገድ አሳየው ቅኸኙ ከፊትህ ጋር ደስታን ትሞላብኛለህ» ያለውን እንዲሁም ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል ፣ ከሽማግሌዎችም ፣ ከካህናት አለቆችም ከጸፎችም ሊጣል ፣ ሊገደልም ከሦስት ቀንም በኋላ ሲነሣ ይገባዋል» በማለት ስለትንሣኤው የተናገረውን ትንቢት በማወቅ ነው ፤ ሁለተኛውም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጠላቶቹ እጅ ተይዞ ተገርፎ በየአደባባዩ ተደብድቦ ተመትቶበመስቀል ላይ ወጥቶ ሙቶ ከተቀበረ በኋላ ምንም እንኳ መቃብሩ ኃያላንና ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያ ቢያዙ ሠራዊት ቢጠበቅም ባዶ ሆኖ በመገ ቱ መነሣቱን በትክክል አረጋግጠዋል ፤ ሦስተኛውም ጌታችን ኢየሱስክርስቶስ በአርባ ቀናት ውስጥለወንዶችና ለሴቶች ፣ ለብዙ ሰዎችም በአንድነትና በየግላቸው በቀንናበሌሊትም በቤትም በውጭም እየተገለጸላቸው እያነጋገራቸው ከእነርሱ ጋር በመመላለሱ ፣ በመራመዱ በመዳሰሱ ፣ የዓይን ምስክሮች ሆነዋል ።

ከዚህም በቀር ከመካከላቸው በላ ከተገለጠላቸው አንሥቶም እስካረገበት ጊዜ ድረስ ብዙ ጊዜያት በመካከላቸው እየተገኘ ሰላም ለእናንተ ይሁን እያለ አጽናናቸው ። በተነሣበት ዕለት ለመግደላዊት ማርያም ። ለሌሎች ሴቶች ፤ ለቅዱስ ጴጥሮስ ፣ ለቀለዮጳና ለአንድ ደቀ መዝሙር በኤማሁስ መንገድ ፣ ከቶማስ በቀር ለአሥሩ ሐዋርያት በአንድነት ሳሉ ፤ በስምንተኛው ቀን (ዳግም ትንሣኤ) ለሐዋርያት ሁሉ ፣ ከዚሁም ቀጥሎ ለሰባቱ ሐዋርያት በገሊላ ባሕር ዳር፤እንዲሁም ለአምስት መቶ ሰዎች ፣ ለያዕቆብ ፣ ወደ ሰማይ ሲያርግ ለቅድስት እናቱና ለሐዋርያት በሙሉ ፣ ካረገ በኋላ በደማስቆ ለቅዱስ ጳውሎስ መታየቱን እንገነዘባለን ።

በዘረ ትንሣኤው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ መሆኑን በእርሱ ያመኑትም ሁሉ በእርሱ ደም መዳናቸውን (መጽደቃቸውን) በክርስቶስ ክርስቲያን ተብለው መጠራታቸውን ፤ የእግዚአብሔር ልጆች መ ላቸውን ያረጋግጣል ። ይኸውም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮማ ምእመናን በጽሑፍ ሲገልጽላቸው ። ይህም ወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለተወለደ እንደቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት የተነሣ በኃይል የእግዚንአብሔር ልጅ ሆኖ ስለተገለጠ ስለልጁ ነው እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» ይልና እልፍ ብሎ «ስለእኛም ነው እንጂ ስለበደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለማጽደቅም የተነሣውን ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን መነሣቱን ለምናምን ለእኛ ይቈጠርልን ዘንድ አለው» ። እንዳለው ሁሉ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዘረ ትንሣኤነት አሁንም ለምናምንሁሉ ተስፋችንቤዛችን ኃይላችንና ጽናችን ነው ።

# ፓትርያርኩ ለትንሣኤ በዓል ያስተላለፉት ቃለ ምእዳን

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ፤—አሜን

በገጠርና በከተማ የምትገኙ ምእመናን የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ለማስከበር ነፃነትዋንና አንድነትዋን ለመጠበቅ በመሐል አገርና በጠረፍ በባሕርና በየብስ በሥራ ላይ የተሠማራችሁ ሠራዊት በሕመም ምክንያት በሐኪም ቤት ያላችሁ ኢትዮጵያውያን ወገናች በሙሉ !

ስለ ሰው ልጅ ቤዛ ሆኖ በመስቀል ላይ የሞተውና ሞትን ድል አድርጎ የተነሣው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም አደረሳችሁ!

"ክርስቶስ ሞተ በእንተ ኃጢአትነ - - - ተቀብረ ወተንሥአ እመ ሣልስት ዕለት በከመ ይቤ መጽሐፍ — መጽሐፍ እንደተናገረ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ ተቀበረ በሦስተኛውም ቀን ተነሣ" (፩ኛ ፣ ቆሮ ፣ ፲፭ ፣ ፫)

የሰው ልጅ በመጀመሪያ ሲፈጠር ሕማምና ሞት ሳይኖሩበት ለዘለዓለም በሕይወት እንዲኖር ነበር። ነገር ግን በነፃ ፈቃዱ ተመርቶ የፈጣሪውን ትእዛዝ ተላለፈ፣ በዚህም ምክንያት ኑሮው ሕማምን ፃዕርን ጋርን ጉስቁልናንም የተመላ ሆነ ፣ ሞተ ሥጋና ሞተ ነፍስም ተፈረደበት ። ነገር ግን የሰው ልጅ ለዘለዓለም በሥቃይ እንዲኖር እግዚአብሔር አልፈቀደም ። ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው የባሕርይ ልጁን ለሞት አሳልፎ በመስጠት ሊያድነው ፈቀደ ።

በዚህም መሠረት ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሰው ሆኖ በዚህ ዓለም ፴፫ ዓመት ከኖረ በኋላ ስለ ሰው ልጆች ቤዛ ሆኖ መከራ መስቀልን ተቀበለ በመስቀል ላይ ሞቶ ተቀበረ በሦስተኛውም ቀን መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ድንጋይ አንሡልኝ ሳይል በታላቅ ኃይልና ሥልጣን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፡ ሞትን በሞቱ ደመሰሰ በመቃብር ውስጥ ለነበሩት ሕይወትንና የዘለዓለም ዕረፍትን ሰጠ በሲኦል ጨለማ ለነበሩ ሁሉ ብርሃነ ትንሣኤውን አበራ ። በዲያብሎስ ሥልጣንና አገዛዝ ሥር ሆነው ይሠቃዩ ለነበሩ ሁሉ ነፃነትን አበሠረ የዲያብሎስንም ሥልጣን ሻረ ። የክርስቶስን ሲቃዮች (ሲቃልያን) ፈርተው በዝግ ቤት የነበሩ ደቀ መዛሙርቱ "ሰላም ለሁላችሁ ደስ ይበላችሁ አስታረቅሁአችሁ" በማለት የሰላም ጌትነቱን ገለጠ በትንሣኤው የሰው ልጆችን ትንሣኤ ሁሉ አረጋገጠ ።

የክርስቶስ ትንሣኤ ፤— ለክርስቲያን ሃይማኖትና ተስፋ መሠረት ነው ፤ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችበት የማይናወጥ ጽኑዕ መሠረት የክርስቶስ ትንሣኤ ነው ፤ ሐዋርያት ወንጌልን ማስተማር ምእመናንን ማሰባሰብ የጀመሩ የተነሣው ክርስቶስን ካዩ በኋላ ነውና ።

የክርስቶስ ትንሣኤ፤—የሰው ልጅ ከሰይጣን ባርነትና ከኃጢአት ቀንበር ነፃ የወጣበት ወደ ቀደመ ክብሩ የተመለሰበት ወደ ገነት የገባበት ሞት ድል የሆነበት በጠቅላላ የዓ



www.ethiopianorthodox.org

ለም የድኅነት ሥራ የተፈጸመበት ነው ።

ዳዊት በመዝሙሩ "እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት ፣ በርስዋ ፈጽሞ ደስ ይበለን" መዝ ፩፻፲፯ ፣ ፳፬) በማለት አስቀድሞ እንደተናገረ ክርስቶስ በተነሣባት በዛሬዋ ዕለት ከሞትና ከመቃብር በኋላ ትንሣኤና ሕይወት መኖራቸው ስለተረጋገጠ የሰው ልጆች ደስታ ፍጹም ሆኖአል ፣ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርትም፦ በክርስቶስ ሞት አዝነው ተስፋ ቆርጠው ሳሉ "ወተፈሥሑ አርዳኢሁ ሶበ ርእይዎ ለእግዚእነ በሣልስተኛው ቀን በዛሬው ዕለት ተነሥቶ ጌታችንን ባዩት ጊዜ ደስ ብሎአቸዋል (ዮሐ ፣ ፳ ፣ ፳)

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ክርስቶስ የተነሣበት የዛሬው ዕለት ፍጹም የደስታ ቀን መሆኑን ሲገልጥ" ማንም ሰው በዚህ ቀን አያልቅስ ፣ ይህ ቀን የይቅርታ ፣ የደስታ ፣ የሰላምና የዕርቅ ቀን ነውና ማንም ሰው አይፍራ የክርስቶስ ትንሣኤ ከሞት ኃይል ነፃ አውጥቶታልና" በማለት ያስተምረናል (ዮሐ ፣ አ ፣ ወ) ።

እኛም "ዮም ፍሥሐ ኮነ በሰንበተ ክርስቲያን እስመ ተንሥአ ክርስቶስ እሙታን ፦ ዛሬ በክርስቲያን ሰንበት ደስታ ሆነ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ አልና" እያልን እንዘምራለን በትንሣኤው ያገኘነውን መንፈሳዊ ደስታችንን እንገልጣለን ። ለምእመናን ሁሉ የትንሣኤውን ብርሃን እያበራን "ክርስቶስ በእውነት ተነሥቶአል" እያልን ትንሣኤውን እንመሰክራለን ።

የተወደዳችሁ ምእመናን ሆይ!

በነገው ዕለት የሰው ልጆች ትንሣኤ የተረጋገጠበት የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ትንሣኤ ስናከብር ከፍተኛ ማስተዋል ልናደርግበት የሚገባ ነገር አለ ይኸውም የሀገራችን ሰላምና አንድነት የሕዝባችን ደኅንነት ጉዳይ ነው ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ቃለ በረከት ሲያስተላልፉ



ለአንድ ሀገር ሥልጣኔና ዕድገት ልማትና ብልጽግና ለኅብረተሰቡም የተሻለ ኑሮና መልካም ጤና መሠረቱ ሰላም ነው ። ያለ ሰላም በዐላትን ማክበርና መንፈሳዊ የአምልኮት ሥርዓትን መፈጸም አይቻልም ። ጦርነት አንድን ሀገር ያለ ምንም ቅርስ ፣ ያለ አንዳች ታሪክ ከማስቀረቱም በላይ የሰው ልጆች ዘርን ከገጸ ምድር ያጠፋል ። ኅብረተሰብን እርስ በእርስ ይከፋፍላል ። ከእግዚአብሔርም ይለያል ።

ስለዚህ ከጦርነት ይልቅ ሰላምን ፣ ከመለያየት አንድነትን ፣ ከጥፋትና ከዕልቂት ልማትን ፣ ለመመሥረት መተባበርና መመካከር አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ይገባል ።

የሰው ልጆች በመልካም ሥነ ምግባር እየተመሩ ከእግዚአብሔር ጋር እርስ በእርሳቸው ያላቸውን ኅብረት ካጸኑ ሰላምን መመሥረት ይችላሉ ። ካህናትም ምእመናንም ሁላችሁ ስለ ሀገራችን ሰላም ስለ ሕዝባችን ደኅንነት በኅበረት አዘውትራችሁ ጸልዩ ።

ኢትዮጵያ በውስጥዋ ላሉ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳትሆን በተለያዩ ምክንያቶች ከሀገራቸው ወጥተው በመላው ዓለም ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እናት ሀገራቸው ናት ።

በመሆኑም በውስጥም በውጭም ያሉት አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ስለ ሰላምዋ ስለ አንድነትዋና ስለ ነፃነትዋ እንዲያስቡ ፣ በጸሎትም ወደ እግዚአብሔር እንዲያመለክቱላት በዚህ ዕለት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ታሳስባለች ።

በአሁኑ ጊዜ በዓለም ዙሪያ ተለያይተው የነበሩ የአንድነትን ፣ ተራርቀው የነበሩ የመቀራረብን ፣ ጠቃሚነት በመረዳት አንድነታቸውን እያደሱና እያጠናከሩ ናቸው ። እንደዚህ ላለውም ዓላማ ሰላም ወዳድ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ድጋፋቸውን ሲሰጡ ይታያሉ ።

እንዲሁም ለሀገራችን ሰላምና አንድነት የዓለም ሰላም ወዳድ ሕዝቦችንና የመንግሥታት መሪዎች በጎ ምክርና አስማሚ ሐሳብ እንዲሰጡ ፣ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎችም በጸሎት እግዚአብሔርን እንዲለምኑ ቤተ ክርስቲያናችን ትጠይቃለች ።

ከዚህም ጋር በነገው ዕለት የምናከብረው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዐለ ትንሣኤ የደስታ የሰላምና የመንፈሳዊ ነፃነት በዐል መሆኑን ተገንዝበን ነፃነት ሰላምና ደስታ አጥተው ለሚቸገሩ ወገኖች ሁሉ ማሰብ ይገባናል ።

በተለይም በሀገራችን ውስጥ በተነሣው ጦርነትና በድርቅ ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው መጠለያ አጥተው በከፍተኛ ችግር የሚገኙትን ፣ በዐለ ትንሣኤን በሰበካ ቤተ ክርስቲያናቸው ተገኝተው ለማክበር ያልቻሉ ወገኖቻችንን ልናስባቸው ይገባናል ። በተለያየ ምክንያት ላዘኑት ሁሉ እግዚአብሔር መጽናናትን እንዲሰጣቸው ኀዘናቸውን ወደ ደስታ እንዲለውጥላቸው መጸለይ አስፈላጊ ነው ። በረኀብ በእርዛትና በሕመም ተጨንቀው የበዓሉን ደስታ የማያውቁም ብዙዎች ስለሆኑ ለእነርሱም የፍቅር የርኅራኄ ሥራ ልንሠራላቸው ተገቢ መሆኑን እንርሳ ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሕይወቱን እስከ መስጠት መሥዋዕት እንደሆነልን እኛም በረኃብ በእርዛትና በደዌ ለሚቸገሩት ሰላምና ዕረፍት አጥተው ለሚጨነቁት መሥዋዕት እስከመክፈል ድረስ የችግራቸው ተካፋዮች መሆን ይገባናል ።

እግዚአብሔር ለሀገራችን
ሰላምን ለሕዝባችን አንድነትን
ይስጥልን
በዓሉን የሰላም፣ የደስታ በዐል
ያድርግልን ።



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዳሜ ሥኡር

ቀዳሚት ሰንበት ከሰባት ዕለታት አንድዋን ሰባተኛይቱ ቀንናት ስምዋም ቅዳሜ ቀዳሚት ሰንበት እየተባለች ትጠራለች ይህም ስያሜ እንዲሁ በሰው ፈጠራ የመጣ አይደለም ቀደም ሲል በዘመነ ብሉይ እግዚአብሔር ሕገ ኦሪትን ሲሠራና ፲ቱ ቃላትንም በእጁ ጽፎ ለሙሴ በሰጠበት ወቅት ከ፲ቱ ቃላት አንዷቱና ሰባተኛውን ቀን«አክብር ሰንበት ለእግዚአብሔር አምላክከ» የአምላክህን የእግዚአብሔርን ሰንበት አክብር ስድስቱን ቀን ሥራህን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አርግ ሰባተኛይቱን ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክ ናት በማለት ሰንበት ብሎ ራሱ እግዚአብሔር ሰይሞአታል ።

በዚህም አማካይነት ሕዝበ እግዚአብሔር ተብለው ይጠሩ የነበሩት እሥራኤላውያን ከእግዚአብሔር በተሰጠው አምላካዊ ትእዛዝ መሠረት ሰንበትን ሲያከብርዋት ኑሮዋል ዛሬም ቢሆን በእነሱ ዘንድ ክብርዋ እንደ ተጠበቀ ይገኛል ።

ሕገ ኦሪት ከተሠራ ጀምሮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ስለሰውም ኃጢአት በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እስከ ሞት ድረስ ደርሶ በከርሠ መቃብር እስካደረባት ድረስ ሰንበት በታላቅ ክብር ትከበር ነበር ሰንበት ማለትም ዕረፍት ማለት ነው ።

እንግዲህ ሰንበት የሚለውን ስም ያገኘችው ከእግዚአብሔር ቃል ከሆነ ለምን ቀዳሚት ተባለች የሚል ሰው ቢኖር ቀዳሚት የተባለችበት ምክንያትምራሱየቻለ ምክንያት አለው ይኸውም በዘመነ ብሉይ እሷ ብቻ እንጂ ሌላ ሰንበት ተብላ የምትጠራ ዕለት አልነበረችም ኋላ ግን አምላካችን ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ የተነሣባት ዕለት እሑድ ሰንበት ስለተባለች ሁለት ሰንበቶች ሆኑ ።

ስለዚህ ሰንበት ቀዳሚነትን ይዛ ሰንበት ስትባል እሑድም ሁለተኛ በር የሰባትም ዕለተ እሑድ ግን መንፈሳዊ ዕረፍት ስለ ተገኘባት መከበር ይኖርባታል ሰንበት አምሳልመርገፍ ናት እንጂ እውነተኛ



ዘከመ ተሰቅለ እግዚእነ በመልዕልተ መስቀል

ሰንበት ተባለች በዚህ ምክንያት ነው ቀዳሚት የሚል ቅጽል ልታገኝ የቻለችው ።

በዚህም ብዙ ክርክር ተነሥቶ እንደ ነበር የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ይመሰክራል ክርክሩም ሰንበት ሥጋዊ ዕረፍት እንጂ መንፈሳዊ ዕረፍት አላስገኘችምና ሰንበት አይደለችም በማለት ኃይለኛ ክርክር አስነሥቶ ነበር ።

ነገር ግን ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው ሁለቱም እንዲከበሩ በማዘዛቸው ሁለቱን እናከብራቸዋለን ይህ ብቻ ሳይሆን ፫፻፲፰ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንም ይህንን የሐዋርያትን ሕግና ሥነ ሥርዓት በመከተልና ሕጉን በማጽደቅ ወአግብርትኒ ይትቀነዩ ሐምሰ መዋዕለ ወበዕለተ ሰንበት ወእሑድ ይጸመዱ ለቤተ ክርስቲያን ።

አገልጋዮችም አምስት ቀን ያገልግሉ ቅዳሜና እሑድ ግን የእግዚአብሔርን አገልግሎት ይማሩ ዘንድ በቤተ ክርስቲያን ይዋሉ ምክንያቱም በዕለተ ቀዳሚት ፍጥረታቱን ሁሉ ፈጥሮ በጨረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሥራው አርፎባታልና በዕለተ እሑድም ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶባታልና ሲሉ በ፲፱ኛው አንቀጽ ቁጥር ፺፮፻፳፭ በጽሑፍ አሥፍረውት ይገኛሉ ።በዚህ ምክንያት ሰንበትን ሰንበተ አይሁድ እሑድን ሰንበተ ክርስቲያን በመባል ተለይተው ሁለቱም ሲከበሩ ይኖራሉ ።

እርግጥ እንደ ሐዋርያትና እንደ ፫፻፲፰ ሊቃውንት ሕግና ሥነ ሥርዓት ሁለቱ በትክክል ሲከበሩ አይታዩም ሰንበት እስከ ፮ ሰዓት ድረስ ሥራ ሲሠራባት እሑድ ግን አይሠራባትም እንደ ሐዋርያትና እንደ ፫፻፲፰ ሊቃውንት አባባል ግን ባለቤቶች ይቅሩና የቤት ሠራተኞች ጭምር በሁለቱ ዕለታት እንዳይሠሩ ተደንግጎ ይገኛል ።

ቅዳሜ ሥዑር

ቅዳሜ ሥዑር የተባለችበትም ዋና ምክንያት በቅዳሜ ቀን ማረስ መቆፈር መቁረጥ መፍለጥ ይገባል ማለት ሳይሆን እንደ ፊተኛው የተዘጋውን ሳይከፍቱ የተከፈተውን ሳይዘጉ ማደርና መዋል እንደዚሁም በሽተኛውን ከመጠየቅ መከልከል ተገቢ ስላይደለና በሰንበት ቀን እሥረኞቹን መጠየቅ ተገቢ በመሆኑ እሥረኞችን መጠየቅ በሽተኞችንም መጎብኘት ስለ ተፈቀደ ነው ።

በሌላም በኩል ሰንበት አትጾምም ነበር ጌታ በመቃብር ከዋለባትና ካደረባት በኋላ ግን ስለ ተጾመች ቅዳሜ ሥዑር ተብላለች ፡ ባሰንበት ቀን መጾም እንደማይገባ ያችን ጌታ በመቃብር ውስጥ



ዘከመ ተንሥአ እግዚእነ እምውስተ መቃብር

ያደረባት ዕለት ብቻ ግን መጾም እንደሚገባ በማስመልከት«ወኢይደሉ ከመ ይቁሙ በዕለተ ሰንበት» በሰንበት መጾም አይገባም እግዚአብሔር ከሥራው አርፎባታልና ቅዳሜ ሥዑር ብቻ ግን ልትጾም ይገባል ። የፍጥረቱ ሁሉ ፈጣሪ በመቃብር ውስጥ አድሮባታልና ይላል ፍትሐ ነገሥትአንቀጽ ፲፩ ፣ ቁጥር ፭፻፸፩ ።

ቅዳሜ ሥዑር በመባልዋ እሁንም ቢሆን ቅዳሚት ሰንበት የተሻረች የሚመስላቸው ብዙ ሰዎች እንዳሉ ይታወቃል ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ቢሆን ሰንበትን ባለችበት እንጸጸናት እንጂ እንደ ሻራት ንባብ አናገኝም ።

እንዲያውም ባለችበት ማጽናቱ ሲያረጋግጥ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ካለም በኋላ ሕጉን ሲያጸና እውነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም ብሏል (ማቴ - ፭ ፣ ፲፯—፲፰ ።)

ከዚህ ላይ አንዲት የውጣ አንዲት ነጥብ የሚሉት ቃላት አሠርቱ ቃላት መሆኑንና ከአሥርቱ ቃላትም አንድዋ አክብር ሰንበተ ለእግዚአብሔር አምላክከ የአምላክህ የእግዚአብሔር ሰንበት አክብር የተባለችው ዕለተ ሰንበት ቀዳሚት መሆንዋን ማስተዋል ይገባል ።

አንዳንዶቹ ሰንበትን እንዳይሽሩ ዓርብ ቀን ውኃ የሚቀዱ እንዳሉ የሚታወቅ ነው አንዳንዶቹ ደግሞ ዕለተ እሑድን በማክበርና በማጋነን የሚናገሩ እንዳሉም ግልጥ ነው ። ለምሳሌ ቅዱስ አትናቴዎስ ዕለተ እሑድን በተለየ ስሜት በማክበር ንዑ ናዕብያ ንዑ ንወድሳ ንኡ ናክብራ ንኡ ናብዕላ ለበኵረ በዓላት እንተ ይእቲ ሰንበት ክርስቲያን ቅድስት

ኑ ከፍ ከፍ እናድርጋት ኑ እናመስግናት ፡ ኑ እናክብራት የበዓላትን በኩር የሆነችው ንም የተቀደሰችውን የክርስቲያንን ሰንበት እናክብራት በማለት ከሰንበት አይሁት ለይቶ የተለየ ክብርንም ሰጥቶ ሲያመሰግናት ይሰማል ።

ሐዋርያት በሲኖዶስ ፫፻፲፰ በፍትሐ ነገሥት እንደ ደነገጉት ግን አምስት ቀን እንዲሠሩ ፪ ሰንበታት ግን እንዲከበሩ ነው የሚያዙት ፡



www.ethiopianorthodox.org

የሆነ ሁኖ ቅዳሜ ሥዑር ማለት ወይም ሥኡር የሚል ቅጽል ልታገኝ የቻለችው ፤

፭ኛ/ መጾም የማይገባት ስትሆን በመጾምዋ

፮ኛ/ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስኩብ ውስተ መቃብር ሁኖ ስለ ዋለባት ፤

፫ኛ/ በሽተኞች መጠየቅ እሥረኞችንም መጎብኘት ስለ ተፈቀደ ነው ።

የሁሉ ማሠሪያና ማጠቃለያ ቃል ግን ጌታ ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ያለውን አጽንቶ መያዝ ያስፈልጋል ። የአምላክ ቃል ነውና

ክነፈ ርግብ ማርቆስ

# የተፈጥሮ ጸጋና የተጎርዮ ጸጋ ልዩነት ።

የተፈጥሮ ጸጋ ስንል ራሱ አካላዊ (ሰብአዊ) ሕይወት ከይህ (አካል) በአፍአ የሚገኙ መጠቀሚያዎቹ በጠቅላላ ናቸው ።

አካላዊ ሕይወትም በህጻናዊ አእምሮ ወይም ከአእምሮና በአካል ጉድለት ከአልተገታ በቀር እስከ ጊዜው በግል አእምሮ ሊመራ ስለሚችል ማንም ቢ ሆ ን ራሱን ለመቈጣጠር ከአልፈቀደ በቀር በሕገ ወጥነት እንኳ ሳይቀር ሊጠቀምበት ይችላል ።

የተፈጥሮ ጸጋ ባሕርይ ተፈጥሮታዊ ጠባይእን ጠብቆ በአካልም በዕውቀትም የሚያድግ ፤ ሀብትም ድህነትም ፤ ሕማምም ጤንነትም ፤ ትሩፋትም ርትዕም ጽድቅም ኃጢአትም የሚስማሙት (የሚፈራረቁበት) ከተፈጥሮ ሕግ ውጪ የሆነ ለውጥ የሚያመጣ ሥራው ሁሉ በተፈጥሮ ሕግ ውስጥ የተወሰነ ፤ ተአምራታዊ ግብር ድርሻው የአልሆነ ፤ ሥጋዊ ዕድሉም በአለው ዕውቀትና ችሎታ መጠን የተለካ ነው ።

የተጎርዮ ጸጋ የምንለው ደግሞ ዕድልተኞች በጊዜው ወይም የአለጊዜ በጸጋ ብቻ ሊመረጡ የሚችሉበት ዕድል ነው ።

በጊዜው ስንል በአካልም ሆነ በአእምሮ ከአደጉበኋላ አጋሬቸውን (ሚናቸውን)ለመለየትና ራሳቸውን በራሳቸው ለመምራት በሚችሉበት ወቅት ፤

የአለጊዜ ስንል ደግሞ ከልደት በፊት ወይም ሊመረጡበት ከማያስችላቸው ደረጃ ሁኔታ ላይ ደርሱ አስቀድሞ ማለት ነው ። (ኤር ፩፡፭ ።)

ይህም እግዚአ ብሔር በዐወቀ ለተለዩ (ኅሩያን) ሰዎች የሚሰጠው የተለየ ጸጋ እንጂ ማንም ቢሆን በራሱ ጥረትና ፍላጎት የሚያገኘው ዕድል ሆኖ አንመለከትም ። (ግብ-ሐ ፰-፲፱ ።)

የተጎርዮ ጸጋ ተአምራታዊ እንጂ ጠባይዓዊ ስለአልሆነ በግል አእምሮ መሪነት ብቻ መሣሪያ ለማድረግና በሕገ ወጥነት ለመጠቀም አያስችልም ማለት በዚህ መሣሪያነት ለመጠቀም ሁልጊዜ በእግዚአብሔር መንፈስ መመራት ይኖራል ።

የተጎርዮ ጸጋ ከባሕርያዊ ችሎታ ውጪ የሆኑ ተአምራታዊ ግብራትን ለመሥራት የሚያስችል መንፈሳዊ ኃይል ነው ።

ስለዚህም መንፈስ ብርቱዎች ከሆኑ አካለ ደካሞች ሳይቀር ይታደሉታል የተፈጥሮ ጸጋ ያው በተፈጥሮ የተጎርዮ ጸጋ በተጎርዮ የሚሰጥ ነው የተጎርዮ ጸጋና የተፈጥሮ ጸጋ በተረክቦና በተውህቦ ቢገናኙም በባሕርይ ይለያያሉ ።

የተጎርዮ ጸጋ ኅርየታዊ የተፈጥሮ ጸጋ ጠባይዓዊ ነው ከእነዚህም ሌላ ጸጋ ትሩፋት መኖሩን መዘንጋት የለብንም የትሩፋት ጸጋ ማለትም ሰው በተፈጥሮ በተሰጠው ጠባይዓዊ ጸጋ አእምሮ እየተረዳ ተገቢ አምላካውያን ሥራዎችን በመፈጸም እንዲመረቱ ሆኖ መገኘት ነው ፤

ለመሆኑ ይህ (ትምህርታዊ ሐተታ) ለምን አስፈለገ ቢባል መልሱ እንደሚከተለው ይሆናል ፤

በባሕርዩ አድልዎና ንፍገት የሌለበት እግዚአብሔር ሰውን በተፈጥሮ ጸጋ ምልዐት አበልጽጎ ፈጥሮአል ።

ታዲያ ሰነፍ በዚህ ዕድል በትክክል ሠርቶ በመጠቀም ከድህነትና ከኃጢአት ራሱን ማንሣት ሲቻለው ይህን ቸል በማለት አካሉንና አእምሮውን የአጣ ይመስል እጅ እግሩን አጣጥፎ በመቀመጥ «ከጥዋቱ ከእናቴ ማኅፀን የአልታደልኩትን » እየአለ ተፈጥሮውንና ፈጣሪውን ስለሚያማርር ከዚህ ስሕተት ለማዳን ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ በተፈጥሮ በእናት ማኅፀን (መታደል ወይም አለመታደል) የሚለው አስተሳሰብ በአንድ አንዶቹ ሀሊና እንደሃይማኖት የሠረፀ በመሆኑ ለየዋሃን ስሕተት ተጨማሪ ምክንያት እንዳይሆን ሰባክያን በተጎርዮ ጸጋና በተፈጥሮ ጸጋ መካከል የአለውን ልዩነት ጠንቅቀው እንዲያስተምሩ ለመጠቆም ያህል ነው ።

አዎ የተጎርዮ ጸጋ ለተለዩ ባለዕድሎች የሚሰጥ ተአምራታዊ ባሕርይ የአለው ስጦታ ሲሆን የተፈጥሮ ጸጋ ደግሞ ለሁሉም የሚሰጥ ጠባይዓዊ ባሕርይ የአለው ስጦታ ስለሆነ ለይቶ ማወቅና ማሳወቅ ያስፈልጋል ።

ይህ የሆነ እንደሆነ በአንድ ዘር በኩል ከመሳሳትና ከማሳሳት ለመዳን ስለሚረዳ ኅብረተ ሰብአ



በሥጋም ሆነ በመንፈሳዊ ህልውናው ሁሉ የተምዋላ የኑሮ ደረጃ ሊኖረው ይችላል ።

በመሠረቱ ሃይማኖት ሥርዓትና ባህል በሁሉም ዘንድ በእየገጽታቸው ተለይተው መታወቅ አለባቸው ።

በመንፈሳዊ አስተሳሰብ በኩል ተጠግተው በመምጣት የሚጎዱትን ምክንያቶች መከላከልና ማስወገድ የመንፈሳውያን አባቶችና መምህራን ድርሻ ነው ።

ገና በእናታቸው ማኅፀን ሳሉ የተመረጡ እንደነበሩ ብናነብና ብናውቅም ተአምራታዊ በሆነው በተጎርዮ ጸጋ መደብ በኩል መመልከት እንጂ ጠባይዓዊ በሆነው በተፈጥሮ ጸጋ እንደሆነ ማሰብ የለብንም ። ሰው ራሱ በተሰጠው የተፈጥሮ ጸጋ ራሱን በራሱ ለማሻሻል ስለሚችል ከድህነትም ሆነ ከኃጢአት ራሱን ነጻ አድርጎ በብዕልና በጽድቅ የበለጸገ ሊሆን ይችላል ።

ይህም ማለት ለሀብትም ሆነ ለድህነት ለጽድቅም ሆነ ለኃጢአት ዕድል ከራስ ሥራ እንጂ ከተፈጥሮ (ከማኅፀን) አይደለም ማለት ነው ።

ሆኖም ለመልካም ነገር በመልካም መቅናት ፣ ቀንቶም ለመምሰል መሞከር ክፉ ባይሆንም የእግዚአብሔር በረከታዊ ጸጋ በአንድ አቅጣጫ የሚታይ ጠባብ ነገር በአለመሆኑ ለራስ በተሰጠ ዕድል ሠርቶ ለመታደል መሞከር እጅግ የበለጠ ጠቃሚ ነው ።

ሰው ሁልጊዜ በግላዊ የተፈጥሮ ችሎታው መጠን ማግረጥ ማሻሻልና ሠርቶ መታደስ ከራስ እጅ (ሥልጣን) የሚገኝ ባሕርያዊ ስጦታ መሆኑን መዘንጋት የለበትም ።

አዎ መልካም ሆነ ክፉ ማናቸውም ዕድል ሁሉ በተፈጥሮ በመስጠት ተወስኖ የሚቀር የሚመስላቸው ሃይማኖታዊ መሳይ የሥራ ደካሞች መኖራቸውን አንጠራጠርም ።

እንዲህም ለማለት የአስደፈራቸው የተጎርዮ ጸጋንና የተፈጥሮ ጸጋን ልዩ ነት ለማወቅ የአላቸው አስተሳሰብ ጠለቅ የአለ ከአለመሆኑ የተነሣ ይመስለኛል ።

ከዚህም ሌላ ከሕገ ተፈጥሮ ጋር የማይጎዳኙ አንድ አንድ ነጥብ ቃሎችን ወስዶ በመጠቀም የተፈጥሮ አስተሳሰብ ሊሆን ይችላል ።

ቀደም ሲል እንደዛሬ ሣይንስ በአልጎለመሰበት ጊዜ አንድ ሰብአዊ ፍጡር ቅርጸ ህዋሳትን አሟልቶ ሊገኝ የሚችለው በእናቱ ማኅፀን ሳለ በ፵ ቀኑ እንደሆነ ይታመን ስለነበር በዚህ ምክንያት ዕድል ጭምር አብሮ እንደሚቀረጽ በማስመሰል ጽሑፍ ትተው የአለፉ ደራስያን አይታጡም ይሆናል ።

ሆኖም ሰው ልባዊና ተመራማሪ ባለአእምሮ ፍጡር እንደመሆኑ መጠን ሳይመርጥ የአየውን የሰማውንና የተቀበለውን ብቻ ተጭኖና እንደሃይማኖት ጠብቆ መኖር የለበትም ።

እንዲያውም ነገሩ ከመሠረቱ ሳይሆን ከጊዜ በኋላም ሥርዋጽ የገባ ግላዊ ሀሳብ ቃል ሊሆን ስለሚችል ከሕገ ተፈጥሮ የሚቃረነው ድርሳን ሁሉ በአንድ ገጽታ ብቻ መመልከት አይኖርብንም ።

ለምሳሌ ትዳሲ አትናቴዎስን ፩፻፲፪ ቁጥር ላይ ብንመለከት እግዚአብሔር ማናቸውንም ነገር ከመሆኑ አስቀድሞ የሚያውቅ መሆኑን እንጂ ዕድል ወስኖ የሚፈጥር መሆኑን አያስረዳንም ።

እግዚአብሔር የተበገረውን አካል ቀርቶ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ እንኳ ሊሆን የሚችለውን ሁሉ የሚያውቅ እንደመሆኑ ማንም ሰው ከጊዜ በኋላ መልካም ሠርቶ የሚጠቀም ክፉ ሠርቶ የሚጎዳ ትጉህ ሆኖ የሚበለጽግ ሰነፍ ሆኖ የሚደኸይ መሆኑን ገና በእናት ማኅፀን ያውቃል ቢባል የሚያስደንቅ አይሆንም ።

ያለዚያስ ጻድቁን ለጽድቅ ኃጢአተኛውን ለኃጢአት ፣ ሀብታሙን ለሀብት ድሃ ውን ለድህነት ዕድል (በተፈጥሮ) በመወሰን ይፈጥራል ቢባል ዘኢያደሉ ለገጽ የተባለ እግዚአብሔርን አድላዊ ማድረግ በሆነ ነበር ።

ማናቸውም ነገርና ሁኔታ ሁሉ ከችሎታው በታች እንደሆነ እናምናለን ፤ ነገር ግን ለሥራው ይዘትና አፈጻጸም ሁሉ ደግሞ ሥርዓት እንዳለው እናውቃለን ፤ አብዛኛውን ጊዜ እንደማስረጃ እየአደረጉ በመውሰድ የሚጠቀሙ በት ኃጢአተኞች በእናታቸው ማኅፀን ተለዩ (ተነከሩ ኃጥአን እማኅፀን የአለውንና የመሳሰለውን ንባብ ነው ። (መዝ ፶፯/፶፰/፫

ይህንም ቀጥታ ንባቡን ብቻ በመውሰድ ለመጠቀም የምንፈልግ ከሆነ ምሥጢሩን ከመሳታችንም ሌላ ሕገ ተፈጥሮን ስለምንቃወም ከትልቅ ስሕተት ላይ እንወድቃለን

ትክክለኛው ትርጓሜ ግን ክፉ አድራጊዎች (ኃጢአተኞች) ከወላጆቻቸውም ሆነ ከአካባቢያቸው ሳያዩና ከማንም ከማን ሳይማሩ ከሕሊናቸው አንቅተው ኃጢአት መሥራትን እንደቻሉና እንደሚችሉ ያረጋግጥልናል እንጂ ፈጣሪ ማንንም ቢሆን የኃጢአትና የድህነት ቁራኛ አድርጎ እንደሚፈጥር እያስተምረንም (ማቴ ፲፱-፴፩

«የምምረውን እምራለሁ ይቅር የምለውንም ይቅር እላለሁ ወይም» የፈቀደውን ይምራል የፈቀደውን ያስጨንቃል «ለዘፈቀደ ይምህር ወለዘፈቀደ ያአቅብ ማለት እግዚአብሔር የበላይ ባለሥልጣን የሌለበት ይግባኝ የማይጠየቅበት መሆኑን ያስረዳል እንጂ ፍርድ ያዛንፋል ማለት አለመሆኑን ለማወቅ ሩቅ አይሆንም ። (ዘጸ-፴፫-፲፱)

«ትልቁ ለትንሹ ይገዛል » ማለትም ትራኔም ሆነ መሸናነፍ በሰው ባሕርይ የአለ እንደመሆኑ መጠን ከጊዜ በኋላ ሊሆን የሚችለውን ዐውቆ ተናገረ እንጂ «ትልቁ ለት



www.ethiopianorthodox.org

ንሹ ይገዛ» ብሎ ትእዛዝ አልሰጠም (ዘፍ ፳፫· ፳፭-፳፫ )

«ያዕቆብሃ ፈተወኩ ያዕቆብን ወደድኩ ኤሳውን ጠላሁ» የአለውም ከጊዜ በኋላ ማለት ሁኔታቸው ከገብራቸው ከተገለጠ ፀኋላ የተነገረ ቃል ስለሆነ ያዕቆብ ፀሥራው ተወደዶ ይሆናል ኤሳውም በግብሩ ተጠልቶ ይሆናል ። (ሚል. ፩-፱)

አለዚያስ እግዚአብሔር ለደጉ ይፈርድበታል ለከፉው ይፈርድለታል (ጻድቁን ተኮንን ኃጢአተኛውን ጽደቅ ብሎ ለመፍረድ ይችላል ወይም በተፈጥሮ የሠራውን ሥርዓት ያፈርሳል የሰጠውንም ፤ መብት ይነሣል ማለት በሆነ ነበር ።

እንዲህም ከሆነ «ኃጢአተኛ ወደንሥሐ ተመልሶ ይድን ዘንድ ቀንን ያስፋል ፤ የኃጢአተኛን ድኅነቱን እንጂ ሞቱን አይፈቅድም» የተባለለት እግዚአብሔር ሰውን የድህነትና የኃጢአት ባለዕድል አድርጎ ይፈጥራል ተብሎ መተቸት አይገባውም ።

በዚህ ፈንታ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ራሱን በራሱ እንዲመራ እንዲገዛና እንዲቆጣጠር ሙሉ ሥልጣንና ችሎታ ሰጥቶ በመፍጠሩ ቅንዓትና ምቀኝነት የሌለበት ሊጋስ ባሕርይን መገንዘብ ይገባል ።

ይህ ሳይሆን ኑሮ ሰው የበጎ አድራጎቱ ዋጋ ሊቆጠርለት የክፉ አድራጎቱ ፍጻሜ ሊቀርብበት ባልቻለም ነበር ። (ማቴ ፳፭-፵፮)

እንግዲህ «በ፵ ቀን ከእናት ሆድ መታደል የሚለው ቃል ዐዋቂዎች እየዐወቁ የስንፍና መጋረጃ የሚያደርጉት ፤ የዋሃን ሃይማኖት መስሎአቸው በየዋህነት የሚጠቀሙበት ኢአማናዊ ቃል እንጂ በተፈጥሮ ጸጋ ውስጥ ቦታ የለውም ።

እንደነዚህ የአሉት ሰዎች በመጀመሪያው ደረጃ (በተሰጣቸው የተፈጥሮ ጸጋ ሠርተው ለመጠቀም ከአልታመኑ በሁለተኛው ደረጃ (በተጎናርዮ ጸጋ) ይልቅ ይሠራሉ ተብሎ እንዴት ሊታመንባቸው ይችላል? (ሉቃ ፲፮-፲፱)

እንዲህም ከሆነ በሁለቱም ደረጃዎች በኩል ውጤት አላገኙም ማለት ዜሮዎች ናቸው ።

የተጎናርዮ ጸጋ ዕድልተኞች እንኳ በተለይ ከተሰጣቸው ዕድል በቀር በርትዓዊ ግብር ሠርተው ከመጠቀምና ወገናቸውን ከመጥቀም የተገቱበት ጊዜ የለም ።

እነሱ የተለየ ብልጫ ድርሻ ቢኖራቸው ከኃጢአታዊ ግብር ለመከልከልና በተእምራታዊ ግብር ለመጠቀም መቻላቸው ነው ።

ይህ በእውነትም ከተፈጥሮ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ልዩ ረድኤት የሚጠበቅ ነው ።

ለማስረጃ ያህል እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ብንወስድ ከሰብአዊ ባሕርይ የተለዩ ዕድሎች እንደነበርዋት እናንብባለን ፤ እኒህም ተደንግሎ ሕሊናና ወሊድ በድንግልና ናቸው ።

ይህም ከሌላዎቹ የተጎናርዮ ጸጋ ዕድልተኞች ሁሉ ልዩ የሚያደርጋት የጸጋ ስጦታ ነው ።

እንዲህ ከሆነ በተፈጥሮ (በማኅፀን) መታደል የሚለውን ቃል ሳናጻምጥና ቦታ ሳንሰጥ የአለማወላወል በተሰጠን ጸጋ ሠርተን ለመታደል እንችል ዘንድ የተጎናርዮ ጸጋንና የተፈጥሮ ጸጋን ባሕርይ ምንነት ለይተን ዕንወቅ ።

ንቡረ እድ ኤዎስጣቴዎስ

የሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አስተዳዳሪ

## እናትህ እነኋት ።

ይህ ቃል ፀዕለተ ዓርብ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ የተናገረው የአደራ ቃል ነው ። ለምሳሌ ሰው ሰውኛውን የኬድን እንደሆነ ደህም ሆነ ሀብታም በሚሞትም ጊዜ የኑዛዜ ቃሉን በዙሪያው ለተሰበሰቡት ዘመዶቹ ናለሚያምናቸው ሰዎች የእናቱን ነገር አደራ በተቻላችሁ ሁሉ እርዷት ደግፏት መከራ ኀዘን በደረሰባት ጊዜ አጽናኗት የደስታዋም ሆነ የኀዘኗ ተካፋይ እንድትሆኑ አደራ ሲል ተናዞ ይሞታል ። ሰዎቹ ቋምነገረኞች ከሆኑ የተጣለባቸውን አደራ ከመጠበቅ ወደኋላ አይሉም ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በሀገሩ ልማድ መሠረት ለሚያፈቅረውና ለሚወደው ለወንጌላዊው ዮሐንስ (እናትህ እነኋት ሲል ለድንግል ማርያምም እነሆ ልጅሽ በማለት የአደራ ቃሉን ለሁለቱም አስተላልፏል ። ጌታችን ይህንን ቃል ያስተላለፈበት ያለምክንያት አይደለም ። ፴፫ ዓመት ከ፫ ወር በዚህ ዓለም በተመላለሰበት ጊዜ በእሱ ምክንያት በእናቱ በድንግል ማርያም የደረሰባትን መከራና ችግር ኀዘንንና ግፍ ፤ ስደትና ረሀብ እንዲሁም ብቸኝነት ስለሚያውቅ ነው ።

ከደረሰባት መከራ ጥቂቶቹን ብንጠቅስ ክርስቶስ ተወልዶ ሁለት ዓመት ሲሞላው የኢየሩሳሌም ገዢ የነበረው ታላቁ ሄሮድስ ሰማያዊ ዙፋኑን ትቶ ተሰቅሎ ሞቶ በሦስተኛ ቀን ተነሥቶ ዓለምን ለማዳን የመጣ መሆኑን ባለማወቁ በእሱ ምክንያት በቤተ ልሔም ዙሪያ የሚገኙትን ሕፃናት ተፈልገው እንዲገደሉ አዘዘ ።

በዚህ ጊዜ መልአኩ ለዮሴፍ «እናቱንና ሕጻኑን ይዘህ ወደ ግብጽ ኺድ» ባለው መሠረት ከታዘዘው መዓት ለማዳን ስትል ብዙ ተንከራተተች ። በየመንገዱም ወንበዴዎች ባየች ቁጥር ሊገድሉት ነው እያለች ተጨነቀች ። ተቸገረች ። ይህንንም መከራ በየጊዜው የምታስበው አረጋዊው ስምዖን ሕፃኑን ታቅፎ ከእርጅና በታደሰበት ጊዜ «እነሆ የብዙዎች ሐሳብ ልብ ይገለጥ ዘንድ ይህ በእስራኤል ላሉት ለብዙዎች ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ለሚቃወሙትም ተሹሞዋል ብሎ ሕፃኑን ካመሰገነ በኋላ ወደእናቱ ወደድንግል ማርያም ፊቱን ዘወር አድርጎ በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል ሲል ትንቢት ተናገር ስለነበረ ነው ። (ሉቃ ም. ፪. ፪—፴፭ ።)

ይህ ነገር ከባድ በመሆኑ በልቧ ተጠባበቀው ነበር ። (ሰይፍ ሁለት አፍ ስላለው ጅማትንና ቅልጥምን እስኪለይ ድረስ ይወጋል ። ያቆስላል ነቢዩ እንደተናገረው መከራውም እንደ ሰይፍ ሆኖ ሥጋዋንና ነፍሷን መንፈሷንም ጭምር ሲያስጨንቃት ልቧንም ሲያቆስላት ኖሯል ። እየተዘዋወረ በሚያስተምርበት ጊዜም ከወንጌሉ እንደ ምንረዳው ሊይዙት ዝድንጋይ ሊወግሩት ፤ ሊገድሉት በሚፈልጉበት ጊዜ ሁሉ ሕሊናዋን እንደሰይፍ ያቆስለው ነበር ። የደረሰባትን መከራ የተገነዘበ አንድ ሊቅ «እመከራቲሃ ኪሩቤል አርባዕቱ ፤

ገጸ ሰብእ አሐዱ ውእቱ «አራት ከሆኑት ከኪሩቤል መከራዎቿ አንዱ የሰው ፊት ነው ብሎ ተቀኝቷል ።» (የግእዝና የአማርኛ ቅኔያት ዋዜማ ቅኔ) የሥነ ጥበብ ቅርስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚ/ር ካሳተመው መጽሐፍ የተወሰደ ።

እንዳለውም ልጅዋን ይዛ በተሰደደችበት ሥፍራ ሁሉ የሰው ፊት እንደ እሳት አቃጥሏታል ። ገርፏታል ፤ መጣላትንና መናቅን አትርፏታል ። አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም ድርሰቱ በቁ. ፩፻፳፭ «ድንግል ሆይ ከዓይኖችሽ የፈሰሰውንና በተወዳጁ ልጅሽ ላይ የወረደውን መራራ እንባ አሳስቢ ።» ሲል ተናግሯል ። የእንባ ብዛት ዓይንን ያቀላል ። ፊትን ያቃጥላል ከዚህ የበለጠ መከራ የለም ።

በመጨረሻም ያ ሲታሰብበት የኖረችውና አረጋዊው ስምዖን በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል ያለው በጸሎተ ሐሙስ ለዓርብ አጥቢያ ከእኩለ ሌሊት ጀምሮ የሮም ጭፍሮች መብራትና ገመድ ይዘው ሙሉ ትጥቅ ታጥቀው ክርስቶስን ያዙት ከሚጸልዩበት ከጌቴሴማኒ እሥረው ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደቀያፋ አዳራሽ ወሰዱት ። ሳይበድል እንደበደለኛ ተቆጥሮ ሲነጋ ወደጲላጦስ ተወሰዶ ። እንደ ኃጢአተኛ ከእሱ ፊት ቆሞ ለምርመራ የቆመበትም ቦታ በእብራይስጥ ገበታ በግሪክ ሊቶስትራ በእኛ ጽፍድፍ ይባላል ። ጲላጦስም እንዲገረፍ ፈረደበት ካስገረፈውም በኋላ አንድም ኃጢአት አላገኘሁበትም ብሎ አሳልፎ የሰጠው በዚሁ ቦታ ነው ።(የዮሐ.ወ. ም. ፲፱ ፤ ፩—፯ ።)

ቀጥሎም ጌታችን ከሚሰቀልበት ከመስቀሉ ክብደት ከመከራው ጽናት የተነሣ ሊሸከመውስ ሳልቻለ ወደቀ ስምዖን ቀሬናዊ ከእርሻው ወደቤቱ ሲመለስ ጭፍሮች አግኝተውት መስቀሉን አሸከመውታል(ማር ፲፭ ፤ ፳፩)እናቱ ቅድስት ማርያምም ከቅዱሳት አንስት ጋር እያለቀሰች አብራት ትጓዝ ነበር ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመስቀል ሕማም ጽናት የተነሣ የደም ወዝ አለበት ሳለ እያለቀሱ ይከተሉት ከነበሩት ቅዱሳት አንስት መካከል አብሮ ቅላየተባለች መልካም ሴት በማዘንና በመራራት ፊቱን በነጭ መሐረብ ጠረገችለት ወዲያውም ለበጎ ሥራ ተስፋ ለመስጠትም ሃይማኖቷንም ለማጽናት የፊቱ መልክ በመሐረቧ ላይ ተቀርጾ ቀርቶላታል ይባላል ።

በተጨማሪም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ሚሰቀልበት ቀራንዮ በሚጓዝበት ጊዜ የኢየሩሳሌም ሴቶች እያለቀሱ ሙሾ እያወረዱ ዋይ ዋይ እያሉ ይከተሉት ነበር ። ክርስቶስም መለስ ብሎ ለእኔ አታልቅሱ ለእራሳችሁ አልቅሱ ሲል ነገራቸው እንዲህም ማለቱ በ፸ ዓ/ም በኢየሩሳሌም ላይ የደረሰውን መከራ ሲገልጽ ነው ። » ቅድስት ሀገር ከተሰኘው መጽሔት ቀንጨብ ተደርጎ የተወሰደ በመሆኑ ሙሉውን ታሪክ ከዚያ ማንበብ ይቻላል ።

ቅድስት ድንግል ማርያምም ከቅዱሳት አንስት ጋር ሆና ከጧት ጀምሮ በመስቀሉ አንጻር ቆማ ታዝንና ታለቅስ ነበር ። ወንጌላዊው ዮሐንስም ከመስቀሉ ፊት ለፊት ሆኖ ምርር ብሎ እያለቀሰ ያዝን ነበር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ፊቱን ቀና አድርጎ «እነሆ ልጅሽ እናትህ እነኋት» ሲል ለሁለቱም የአደራ ቃሉን ሰጠ ። (ዮሐ· ም· ፲፱ ፤ ፳፮—፳፯ ።)

ይህንን የተገነዘበው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በጌታችን በኢየሱስ ላይ የተጣለውን ኃላፊነት አደራ አስተምሯል ። እንደተባለውም ያለቤተሰብ ኑሮ እንደማይሟላና ሕይወትም እንደማይሳካ ያስረዳል ። ይህም የእናት የአባቱ የወንድ ም የእኅት ሁኔታ እንዲጠበቅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ ነው ። አንዳንዶቹ ለቤተሰቦቻቸው መዳንና የተሰጡትን አደራ ለመጠበቅ ግዴለሾች ይሆናሉ ። እንዲህ ያለውን ቤተ ክርስቲያናችን አታስተምርም መጽሐፍ ቅዱስም አይደግፈውም ። ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ሆኖ ነፍሱን በሰጠ ጊዜ ዮሐንስን ያለው እነኋት እናትህ ተንከባከባት ጠብቃት አስብላት ፤ ሲል ኃላፊነትን ሰጥቶታል ።





www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ እንደ ዮሐንስ ታማኝ ሊሆን ክርስቲያኖች ሁሉ ቅድስት ድንግል ማርያም የቃል ኪዳን ፣ የመንፈስ ፣ የአደራ እናታችን ሆና እንደተሰጠችንና እኛም የቃል ኪዳንና የአደራ ልጆችዋ ሆነን ተሰጥተናል ። ስለዚህ የአደራ ልጆችዋ በመሆናችን ከክርስቶስ መስቀል ፊት ለፊት ሆነን ካዘንንና ከጸለይን ከሥጋዊውም ከመንፈሳዊው ችግራችን እንደምታላቅቀን የታመነ ነው ።

መዓዛ አስማማው

# ቅዱስ ጊዮርጊስ ሊቀ ሰማዕታት

የቅዱስ ጊዮርጊስ አባቱ አንስጣስዮስ (ዘሮንቶስ) እናቱ ቴዎብስታ ይባላሉ ። የአባቱ ሀገር ቀጰዶቅያ የሚባል ሲሆን የእናቱ የትውልድ ሀገር ደግሞ ፍልስጥኤም መሆኑ በመጽሐፈ ገድሉ ተመዝግቦ ይገኛል ወላጆቹ ክርስቲያኖች ከመሆናቸውም ሌላ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰውንም የሚያከብሩ ነበሩ የቅዱስ ጊዮርጊስ አባት አንስጣስዮስ በዘመኑ ከነበረው ንጉሥ ዱድያኖስ ከፍተኛ የሆነ ሹመት ነበረው በተወለደ በ፳ ዓመቱ አባቱ ስለሞተ የአባቱን ሹመት ለመጠየቅ ወደዱድያኖስ ሄደ ፣ ከንጉሡም አደባባይ ሲደርስ ጣዖት አቁሞ ሲሰግድና ሲያሰግድ አገኘው ቅዱስ ጊዮርጊስ ወደቤቱ ተመልሶ ሄደ ከአባቱ የወረሰውን ሀብት ሁሉ ለችግረኞች አከፋፈለና ወደ ንጉሡ ዱድያኖስ በመሄድ ንጉሡና ሠራዊቱ ተሰብስበው እንዳሉ የሚያመልኩት ፣ የሚወድቁለትና የሚነሡለት ጣዖት የማያድን መሆኑን ገልጾ ሰማይንና ምድርን ለፈጠረ አምላክ መስገድ እንዳለባቸው በአደባባይ ሊሰምቶ ተናገረ ወዲያው ንጉሡ ዱድያኖስ እጅግ በጣም ተናደደና አሳሰረው እንዲደበድቡትም አዘዘ አሽከሮቹም ቅዱስ ጊዮርጊስን ይዘው በጎመድ ይወቁት ጀመር እርሱ ግን ስለጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣት መወለድ መሰቀልና መሞት በሞቱም ዓለሙን ማዳኑን ከመመስከር ወደኋላ አላለም ዱድያኖስ ጠበብቱን አገዞ ጥርስ ያለው እንደመጋዝ ያለ ብረት አሠራና በዚያ እንዲገዘገዝ አደረገ ቅዱስ ጊዮርጊስ ለጊዜው ቢሞትም በፈጣሪው ኃይል ተነሥቶ ማስተማሩን ቀጠለ አጠገቡ ሆነው ሁኔታውን የተመለከቱ ፫፻፷፱ ሰዎች በክርስቶስ ስም አምነው ከተጠመቁ በኋላ ሁሉም በሰማዕትነት አረፉ በዱድያኖስ ሥር የነገሡ ሰባ ነገሥት ነበሩ ፤ የተቀመጡባቸውን ሰባ ወንበሮች አለምልመህ ብታሳየን ሁላችንም በአንተ አምላክ እናምናለን አሉት ቅዱስ ጊዮርጊስ ወደፈጣሪው ቢጸልይ ነገሥታቱ የተቀመጡባቸው ወንበሮች ሁሉ አለመለሙ ነገሥታቱ ግን በክርስቶስ ለማመን አልፈለጉም ሌላ ተጨማሪ ተአምር እንፈልጋለንና ሙት አሥነሥተህ አሳየን አሉት እርሱም ከወንዶችም ከእንቶችም ከሽማግሌዎችም ከልጆችም የተደባለቁ ሙታንን በጸሎቱ አሥነሥቶ ቢያሳያቸው ምትሐት ነው አሉ ።

ብረት ምጣድ በእሳት ላይ ጥደው እንደቆሎ ቆልተው ወደ ደረቅ ጉድጓድ ወርውረው ጣሉት አሁንም ለሁለተኛ ጊዜ ብድግ ብሎ ተነሥቶ የማስተማር ተግባሩን ቀጠለ ዱድያኖስ እየተከታተለ እስከመጨረሻ ድረስ እንዲያሠቃዩት ስለአዘዘ አሁንም ተከታትለው እየደበደቡ ወደ አውድማ ወስደው እንደ እህል በበሬ እግር ካሳሹት በኋላ ሲሞት ሰውነቱን አልመው ደቁሰው ሲያበቁ ይድራስ ወደ ሚባል ከፍተኛ ተራራ አውጥተው በነፋስ አዘሩት በየዛፉ ቅጠል ያረፈው የአጥንቱ ብናኝ እኔ ጊዮርጊስ የክርስቶስ አገልጋይ ባሪያ ነኝ ስለ እርሱም እመሰክራለሁ ፣ ክርስቶስ ስለሰው ልጆች በደል ሞቶ በሞቱ ሞትን ደምስሶ ለሰው ልጆች ዘለዓለማዊ ነጻነትን አጎናጽፎቸዋል ። ስለዚህ የሚያድን ክርስቶስ ነው ከክርስቶስ በቀር ሌላ አዳኝ የለም እያለ መሰከረ ።

እንደሞተ አልቀረም አሁንም ለሦስተኛ ጊዜ ተነሥቶ የማስተማር ተግባሩን ቀጠለ፤ቅዱስ ጊዮርጊስ ተጋድሎውን ሲጀምር ሦስት ጊዜያት ሞቶ እንደሚነሣ ከፈጣሪው ተነግሮት ነበር በዚህ መሠረት ተጋድሎውን ወደማገባደዱ ተቃርቧል አሁን ደግሞ በረኃብ ለመግደል አስበው ምንም ከሌላት ድሃ መበለት ቤት ወስደው ከምሰሶ ጋር አሠሩት እርሱም በጸለየ ጊዜ የታሠረበት ምሰሶ አለመለመና አፈራ ፍሬውንም ተመገበ ለመበለቷም ዕውር ዱዳ ደንቆሮ ሽባ ልጅ ነበራት አምጥታ ቅዱስ ጊዮርጊስፈውሶላታል።ንጉሡ ዱድያኖስ በዚያም በዚያም ቢል ለማሸነፍ ባለመቻሉ ልጁን አጋብቶ ለመንግሥቱ ገብቶ የማስተማር መንገድ በማግኘቱ በጣም ተደስተ ፈቃደኛ መሆኑንም ለዱድያኖስ ስለገለጸለት ወዲያው ወደ ቤተ መንግሥቱ እንዲገባ አደረገ ፤ ቅ· ጊዮርጊስም ከቤተ መንግሥቱ እንደገባ የማስተማር ተግባሩን ቀጥሎ ሲያስተምር የንጉሡ ዱድያኖስ ሚስት ሰምታ በአምላከ ጊዮርጊስ አመንኩኝ ብላ የክርስትና እምነትን ተቀበለች ዱድያኖስ ከአደባባይ ውሎ ማታ ሲመለሱ ሚስቱ እኛ የምናመልከው ጣዖት ዓይን እያለው የማያይ ጆሮ እያለው የማይሰማ እግር እያለው የማይራመድ በመሆኑ ተሳስተናል ከዛሬ ጀምሮ ሰማይንና ምድርን ፣ በፈጠረ በጊዮርጊስ አምላክ አምናለሁ የሚያድን ካለክርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለምና ስትል መሰከረች ።

ዱድያኖስ በጣም ተናደደና በሰይፍ ወገቧን ሰንጥቀው እንዲገድሏት አዘዘ ይኸው ቅጣት ወዲያውኑ ተፈጽሞባት የሰማዕትነት ክብርን ተቀዳጅታለች ከዚህ በኋላ ቅዱስ ጊዮርጊስ ወደ ሰማይ አንጋጦ ይጸልይ ጀመር ፤ ጸሎቱም እሳት ከሰማይ ወርዶ ሰባውን ነገሥታት ከእነሠራዊታቸው እንዲያቃጥላቸው ነበር እግዚአብሔር ጸሎቱን ሰምቶ እሳት ከሰማይ ወርዶ ፸ውን ነገሥታት ከነሠራዊታቸው ጋር አቃጥሏቸዋል ።



ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰማዕተ ልዳ

ቅዱስ ጊዮርጊስ ዕለተ ዕረፍቱ እንደ ቀረበ አውቆ የምሕረት ቃል ኪዳን ለመቀበል ወደፈጣሪው ይጸልይ ጀመር ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ተገልጾ በእኔ አምኖ በአንተ በመማጸን በስምህ ቤተ ክርስቲያን የሠራ መጽሐፈ ገድልህን የጻፈ ያጻፈ የሰማ ያሰማ ስለአምላከ ጊዮርጊስ ብሎ የተራበ ያበላ የተጠማ ያጠጣ የታረዘ ያለበሰ የሠራውን ኃጢአት ሁሉ ደምስሼ መንግሥተ ሰማያትን አወርስዋለሁ ። በማለት ቃል ኪዳን ከሰጠው በኋላ ተሠውሮ ታል (ማቴ ፲፡፵፩—፵፪ ።)

ከዚህ በኋላ ዱድያኖስ በሰይፍ አንገቱን ተቆርጦ እንዲሞት ፈረደበት በዚህም መሠረት ሚያዝያ ፳፫ ቀን በሰይፍ አንገቱን በተቆረጠ ጊዜ ደምና ውኃ ወተት ከአንገቱ ወጥተዋል ሰባት የክብር አክሊላትም ወርደውለታል እነዚህም አክሊላት የሰባት ዓመት ተጋድሎውን የሚመሰክሩ ናቸው እኛም ከሰማዕቱ ረድኤትን በረከትን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘለዓለማዊ ድኅነትን ለማግኘት እንችል ዘንድ እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሳንፈራ ሳናፍር በአደባባይ ስለ ክርስቶስ መመስከር ይገባናል ፤ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ ተብሎ ተጽፏልና ።(ማቴ· ፲፡፴፪)

ቀ·ሲ· ጎሩያን ልሣነ በዛብኅ





www.ethiopianorthodox.org

# ዋና ሥራ አሥኪያጁ በጽ/ቤታቸው ለጋዜጠኞች መ ግ ለ ጫ ሰ ጡ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ዶክተር ማርቆስ ወልደ ኢየሱስ የካቲት ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም በጽ/ቤታቸው ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጥተዋል ። ዋና ሥራ አስኪያጅ መግለጫ የሰጡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የሚመራው ቡድን አውስትራልያ ካምቤራ ላይ በተደረገው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሰባተኛ ጠቅላላ ስብሰባ ተካፍለው ከተመለሱ በኋላ ነው

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት በሰባት ዓመቱ ጠቅላላ ስብሰባ እንደሚያደርግ የታወቀ ነው ። በዚሁም መሠረት ዘንድሮም ከየካቲት ፩ እስከ ፳ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም ድረስ ሰባተኛ ጠቅላላ ስብሰባ በአውስትራልያ ካምቤራ ማድረጉን ዶክተር ማርቆስ ወ/ኢየሱስ አስረድተዋል እንደሚታወቀው ሁሉ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር በ፲፱፻፵፩ ዓ/ም ሲመሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን አባል ሆና መመዝገብዋና በጉባኤ ሁሉ ስትካፈል መቆየትዋ የሚታወስ ነው፤ ባሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያናችን የምእመናኗ ብዛት ከራሺያ ምእመናን ሁለተኛ ደረጃ መያዝ ዋንም ዶክተር ማርቆስ ወልደ ኢየሱስ የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ከመግለጫቸው ጋር አክለው አብራርተዋል ።

ዶክተር ማርቆስ ወ/ኢየሱስ ስለ ስብሰባው መርሐ ግብር ሲያትቱ ማኅበሩ የሚሰበሰብበት ድንኳን ከአራት ሺህ ሕዝብ በላይ እንደሚይዝ ጠቁመው ስብሰባው የተከፈተው ደግሞ በአውስትራሊያ መንግሥት ጠ/ሚኒስቴር እንደነበርና ስብሰባው የተመራውም በአብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ዋና ጸሐፊ መሆኑንም አስታውቀዋል ።



ዋና ሥራ አስኪያጁ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሲሰጡ

ዶክተር ማርቆስ ወ/ኢየሱስ በስብሰባው ላይ ብዙ ተናጋሪዎች እንደነበሩና አብዛኛዎቹም የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች መሆናቸውን ገልጸው እነዚህም ስለመንፈስ ቅዱስ የነበራቸው አመለካከት ከኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የተለየ እንዲያውም ቅር የሚያሰኝ በመሆኑ በጭቅጭቅና በንትርክ ብዙ ጊዜ የወሰደ (ያጠፋ) መሆኑንም አልሸሸጉም ። ይሁን እንጂ ነገሩ ብዙ ውይይት ተደርጎበት ወደአስተማማኝ ደረጃ በመድረሱ እርግጥ ተደርጎበታል ሲሉ ዋና ሥራ አሥኪያጁ ገልጸዋል ።

ዶክተር ማርቆስ ወ/ኢየሱስ ገለጻቸውንበማራዘም ሲያብራሩ ስብሰባው ተጀምሮ እስከ ሚጨረስ ድረስ አባላቱ ጠዋት ጠዋት በየተራ የጸሎቱን ስነ ሥርዓት በመልካም ስነ ምግባር ሲመሩ መሰንበታቸውንና በዚሁም ላይ አባላቱ በመካከላቸው ያሳዩት የነበረው የመግባባት ጠባይ አስደሳች እንደነበረ በትዝታ አስታውሰዋል ።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ስብሰባ በጉባኤው ካሳለፋቸው ጠሳሳት ውሳኔዎች መካከል አንዱ በአውስትራልያ አስተዳደር ውስጥ ስለሚኖሩ ጭቁን ጥቁሮች መብት መከበር ነበር በማለት ዋና ዋና ሥራ አስኪያጁ ሲያስረዱ በአውስትራልያ ነጮች መካከል የሚኖሩ ጥቁሮች በሦስት ደረጃ ይከፈላሉ ካሉ በኋላ እነርሱም አንደኛው ክፍል ምንም እንኳ ተምረው እንደ ነጮቹ ሙሉ ክብርና መብት አግኝተው የሚኖሩ ባይሆኑም ትንሽ በተሻለ ሁኔታ የሚኖሩ ናቸው ሁለተኛው የጥቁሮች ክፍል ደግሞ ቢማሩም ባይማሩም ሠርተው ፣ ማለት ነግደው አትርፈው እንደ ነጮች የፈለጉትን ገዝተው በልታው ጠጥተው ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩ ማለት ነው ፤ ሦስተኛው የጥቁሮች ክፍል አቦርጂናስ የሚባል ጎሳ ነው እነዚህ ጥቁሮች ፈጽሞ የተረሱ (የተዘነጉ) በበረሀ የሚኖሩ ከቁጥር የማይገቡ ምንም የማያውቁ ያልተማሩ ማለት ነው ሲሉ ከማብራራታቸውም በላይ እነዚህም ጭቁኖች የአውስትራልያ መንግሥት ልዩ ትኩረትእንዲያደርግላቸውጉባኤው አበክሮ ከማሳሰቡም በላይ መብታቸው በተገቢ መንገድ እንዲጠበቅ ጥረት ያደርግ ዘንድ በጥብቅ ውሳኔ አስተላልፎአል ብለዋል ።

ዶክተር ማርቆስ ወልደ ኢየሱስ ስለ ኢራቁ መሪ ሳዳም ሁሴን እብሪት እንሥተው ሲያብራሩም ሳዳም ሁሴን ጉባኤው በሰፊው ከመወያየቱም በላይ ሳዳም ሁሴን በእብሪት ተነሣሥተው ኪያዙት አገር ከኩዌት በአስቸኳይ እንዲወጡ ጉባኤው የማያዳግም ውሳኔ ማስተላለፉን በማውሳት ነገር ግን ከኢራቅ የመጡና በጉባኤው መካከል የተገኙት የሃይማኖት መሪዎች (የኦርቶዶክስ ጳጳሳት) ሳዳም ጥፋት የለባቸውምና ከኩዌት ሊወጡ አይገባም ሲሉ በመከራከራቸው ጉባኤው አስገርሞታል ያም ሆነ ይህ ግን በኛየዜና ማሠራጫዎች እንደተነገረውና እንደሰማችሁት ሁሉ ውሳኔው ተግባራዊ ሆኖአል ውሳኔውን ሊያገደው የቻለ ኃይል አልተገኘም ብለዋል ።

ከዚህም ቀጥሎ ከጉባኤው መካከል ስለሴቶች ክህነት መቀበል በውይይት ተነሥቶ ብዙ አከራክሮአል ባንድ በኩል ስለዚሁ ድጋፍ ከፍተኛ ግፊት ቢኖርም በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ ግን ከፍተኛ ተቃውሞና ቅራኔ ፈጥሮ ነበር ካሉ በኋላ ይልቁንም እንዲት እፍሪታዊት ሴት ባሰሙት ከፍተኛ ቅራኔ ማለትሁለት ሺህ ዘመናት አዳመጥናችሁ አሁን ደግሞ እኛን ብትሰሙን ምን አለበት ? ብለው ንግግራቸውንሲጀምሩ ጉባኤው በጭብጨባ ደስታውን ገልጾላቸዋል ብለዋል።

እንዲሁም በሥራ አመራር (በሥልጣን) ወጣቶች መሳተፍ አለባቸው የሚል ሀሳብ ቀርቦ ነበር ከሦስት መቶ አምስት በላይ ሴቶችና ወጣቶች ከማዕከላዊ ኮሚቴ ምርጫ ቢገቡና በከፍተኛ ሥራ ላይ እንዲቀመጡ መደገፍ ቢቻልም በዚሁ አኳያ ጉባኤው የሚያስከትለውን ችግር በመገምገም ከፍተኛ ተቃውሞ አድርጎአል በማለት ዋና ሥራ አስኪያጁ በሰፊው አትተዋል ።

ዶክተር ማርቆስ ወ/ኢየሱስ ዋና ሥራ አስኪያጅ ጉባኤው ለሰባት ዓመት የሚመሩ ማዕከላዊ ኮሚቴ ምርጫ እንዲካሄድ ባደረገው ውድድር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንድ ጳጳስና ዋና ሥራ አስኪያጅ በመመረጣቸው ቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ ዕድል አግኝታለች ብለዋል ። እያይዘውም የማዕከላዊ ኮሚቴ ዋና ፕሬዝዳንት ለመምረጥ በተደረገው ከፍተኛ ጥረት የእስክንድርያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሽኖዳ በአንደኛ ደረጃ ዋና ፕሬዝዳንት ሆነው ተመርጠዋል ካሉ በኋላ ለንኡሳን ኮሚቴዎች በግሩፕ እንዲመረጡ ሆኖ እፍሪቃን በመወከል አንድ ወንድ ቢመረጡ ሴት ካልሆነች አንቀበልም በሚል ምክንያት ብዙ ችግር መፍጠሩን ዶክተር ማርቆስ አመልክተው ከብዙ ንትርክና ጭቅጭቅ በኋላ ምርጫው ጸድቆአል ብለዋል።

የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አርቶዶክሳውያን ፲፩ ቦታ (ሥፍራ) እንዲያገኙ ሆኖአል ። ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ በዚሁ ምርጫ ውስጥ እንደገና ተመርጠው ገብተዋል ካሉ በኋላ ጠቅላላ መግለጫውም በሚቀጥለው ስብሰባ ማለት በመስከረም ወር በቀስታና በርጋታ እንዲታይ በቀጠሮ መተላለፉን ገልጸዋል ። ስብሰባው እጅግ በጣም ጥሩ እንደ ነበርና በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ሌሎቹ ልኡካን መካከል የነበረው መግባባትም የሚያስደስት እንደ ነበረ ዶክተር ማርቆስ እጅግ አድንቀዋል ።

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጋር ለመቀራረብ ለመግባባትና ለመወያየት በተደረገው ሙከራ ጥሩ መልክ ይታይበት እንደነበርና የሚያለያዩ አንዳንድ ምክንያቶች ቢኖሩም በሁለቱ እኅት አብያተ ክርስቲያናት በግልጽ ታውቆየሚወገድበትን መፍትሔ እንዲፈለግለት የጋራ ጥረት እንደሚጠይቅና እስከዚያውም እየግላቸው ጉዳዩን እንዲያጠኑት የተስማሙ መሆናቸውን የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ዶክተር ማርቆስ ወ/ኢየሱስበማስረዳት ዝርዝርመግለጫቸውን ደምድመዋል ።





www.ethiopianorthodox.org

# የሃይማኖት ብዛት ያስከተለው ችግር

ሃይማኖት ከበዛ በሰዎች ዘንድ እርስ በእርስ መለያየትንና አለመስማማትን ከመፍጠሩም ሌላ በየጊዜው ሁከትን ጭቅጭቅን እያስነሳ ፍቅር ሰላም መግባባት እንዳይኖር ያደርጋል ። ይህንንም የተገነዘበው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን አማኞች መምህራን መልካም ትምህርት ሲያስተምሩ ይውላሉ ቢፅ ሐሳባውያን ደግሞ በጨለማ እየመጡ እንክርዳድ ይዘራሉ ማለትን ስለሰማ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልእክቱም ፬፥፬—፮ በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ ፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉ አባት አለ ። ሲል የተለያዩት አንድ እንዲሆኑ እና በመካከላቸውም ሰላም እንዲፈጠር ይህንን መልእክት ጽፎላቸው ነበር ። ከእነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት የወጣ ግን ፀረ ሰላምና ፀረ ሃይማኖት የማኅበራዊ ኑሮ ተቃዋሚ መሆኑን በየመልእክቶቹ ጽፎ አስተምሮአል ቀጥሎም ስለሃይማኖት ብጥብጥና ቤተ ክርስቲያንም ሰላም አጥታ ስለነበረች ፫፻፲፰ ሊቃውንትበኒቅያ ተሰብስበው ከተወያዩ በኋላ ፀረ ሃይማኖቶችን ከቤተ ክርስቲያን ለይተው የሃይማኖት ቀኖና በሆነው በጸሎተ ሃይማኖት ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንና ኃጢአትን በምታስ ተሰርይ በአንዲት ጥምቀት እና ምናለን ሲሉ ለሚነሣው ትውልድ በሲኖዶስ ወስነው አስተላልፈዋል

በ፲፱ኛው ክፍለ ዘመን በመጨረሻና በ፳ ክፍለ ዘመን በመጀመሪያ ግን የሃይማኖት ብዛት በየቀኑ እንደ እንጉዳይ ይፈላ ጀመር ይህንንም ነገር በይበልጥ ሊያስፋፋውየቻለው የአሜሪካን መንግሥት የመተዳደሪያ ሕግ አውጥቶ ከሃያ አምስት በላይ ተከታይ ካገኘ ማንኛውም ሰው የሃይማኖት ድርጅት ሊያቋቁም ይችላል የማቋቋም መብቱ የተከበረ ነው በማለቱ በዚህ ብዙ ሰው ተጠቀመበት በዚህ አኳኋን በዘመናችን ፪ሺ፭፻፹፱ የሃይማኖት ድርጅቶች እንዳሉ እ - ኤ - አ - በ፲፱፻፹፪ ሰኔ ወር ላይ ታትሞ የወጣው ክርስቲያን ሳይንስ ሞኒተር የተባለው የአሜሪካን ጋዜጣ በስፋት አትቷል ። ከእነዚህ መካከል ፩፻፹፱ የክርስትና እምነት ሲሆ ፪ሺ ግን ከክርስትና እምነት ውጪ የሆኑ ናቸው ከእነዚህም አጠር ባለ መልክ ፍሬ ነገሮቹን ጨምቄ በማውጣት አንባቢዎቻችን እንዲረዱት ለማድረግ ነው ።

ሁኔታውም ይህን ይመስላል እነዚህ ሃይማኖቶች አብዛኞዎቹ በአሜሪካ ፣ በሕንድ ፣ በጃፓን ፣ በቻይናና ፣ እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ በእንግሊዝ ይገኛሉ ። ይህም ሲባል ዋና መሠረታቸውን ለማመልከት እንጂ ተከታዮቻቸው በመላው ዓለም እንደተሰራጨ ግልጽ ነው ። በይበልጥም በሽታ ድህነትና ድንቁርና በሚያጠቋቸው ታዳጊ አገሮች በእርዳታ ስም በብዛት ተስፋፍተዋል ። ለምሳሌ በኬንያ ናይሮቢ ከ፫፻ በላይ የሆኑ ልዩ ልዩ የሃይማኖት ድርጅቶች በማዕከልነት ተመስርተው የአፍሪካ አገሮችን በመቆጣጠር ላይ ይገኛሉ ። እንደዚሁም በእስያ ፣ በሊባኖስ ፣ በላቲን አሜሪካ በሜክሲኮ ፣ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ፣ በሩቅ ምሥራቅ በሕንድ በምሥራቅአውሮፖ በግሪክ ፣ በምዕራብ አውሮፓ በእንግሊዝ ፣ በምእራብ ጀርመን በሲውዘርላንድ የሚገኙት ድርጅቶች ልክ እንደ ኬንያ በማእከልነት የሚያገለግሉ ሆነው እናገኛቸዋለን ። ይህንንም ለማወቅ የምንችለው በመጨረሻው ዘመን ጥበብ ፣ ዕውቀት ፣ ሃይማኖት ፣ ፍልስፍና ይበዛል ተብሏልና ።

በዚህም መሠረት አንዳንድ የሃይማኖት መሪዎች ከሚኖሩበት ማኅበረ ሰብ ጋር ያልተስማሙ እንደሆን የራሳቸውን ፍልስፍና መቀየስ ይጀምራሉ እነዚህ ሰዎች እድገታቸው ከሃይማኖት ጋር የተዛመደ በመሆኑ ሰውን የሚስቡበት ልዩ ልዩ መንገድ ማቀድ ይጀምራሉ ከብዙ ስቃይና መከራ በኋላ ዓላማቸው ግቡን መትቶ የሰመረላቸው እንዲሆን የመሠረቱት ድርጅት በጠባቢ ሳይወሰን ዓለም አቀፋዊ መልክ ያለው ብዙ አባላትን ያሰባሰበ በኢኮኖሚ የዳበረ በትምህርት የበለፀገ ራሱን ከመርዳት ባሻገር ሌሎችንም የሚረዳ ይሆናል አብዛኞዎቹ የሃይማኖት ድርጅቶች የሚያ ከናውኑት የበጎ አድራጎት ሥራ እንዲዋደዱና እንዲፋቀሩ ስለሚያደርጋቸው ብዙ ተከታዮች ያገኛሉ ። ለምሳሌ ያህል ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ጥቂቶቹን እንመልከት የድሆች ልጆች ማሳደጊያ ድርጅቶች እጓለ ማውታ ድርጅት ፣ የልጃገረዶች ትምህርት ቤት ፣ የሙያ ማሰልጠኛ ተቋም የአካለ ስንኩላን ማቋቋሚያ ማእከላት ፣ ሐኪም ቤቶች ወዘ ፣ ተ እነዚህን የመሳሰሉትን የሚያቋቁሙበት ዋናው ምክንያት በእርግጥ ማኅበራዊ ኑሮን በተሟላ ሰብአዊ ግልጋሎት ለማስፋፋት ሳይሆን በሃይማኖት ሰበብ እያሳበቡ ብዙ ተከታዮችን ለማፍራት ነው።

እግዚአብሔር አንዲት እምነት አንዲት ቤተ ክርስቲያንና አንዲት ጥምቀት ብቻ እንድንከተል በመጽሐፍ ቅዱስ ደጋግሞ ቢያስተምረንም የእርስ በእርስ አለመጣጣምና አለመመካከር በሊቃውንት መካከል ንትርክ እየተፈጠረ ከላይ የጠቀስናቸው እምነቶች ሊበዙ ችለዋል ። ሊቃውንቱ ሃይማኖት የሚበዛበት ምክንያት ሦስት ዓይነት መንገድ አሉ ። አንደኛ የግል ጥቅምን ለማካበት ፣ የተትረፈረፈ ሀብትን ለመሰብሰብ ነው ። ይህንንም በምሳሌ ብንመለከት በአሜሪካ በካሊፎርኒያ እስቴት የሚገኙ በዓለም የታወቁ በኢትዮጵያም ብዙ ድርጅቶች አቋቁመው የነበሩ ሁለት የወንጌል ሚሲዮናውያን ድርጅቶች ከፍተኛ ፉክክር በማድረግ ላይ ናቸው ። እነዚህም ስማቸው ስለሚታወቅ ከዚህ ስማቸውን መጥቀስ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም የሚያደርጉትም የንግድ ዓይነት ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርስቲ የንግድ ትምህርት ቤት በመክፈት ከክሊኒክ እስከ ዘመናዊ ሆስፒታል በማቋቋም ተከታዮችን በማብዛት አስራትና ሙዳየ ምፅዋትን በመሰብሰብ የታወቁ ፕሮፌሰሮችንና ዶክተሮችን ከፍ ያለ ገንዘብ ሰጥተው በማሠራት ለድርጅቶቻቸው ዝና እያተረፉ ድሀውን ሕዝብ እየበዘበዙ ይከብራሉ ።

ሁለተኛ አንዳንዶቹ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ደንብ ከአለቆቻቸው ጋር ስምምነትን ሲያጡ በውግዘት ይለዩዋቸውና ሲያሳድዱዋቸው ከመጨነቃቸው የተነሣ እራሱን የቻለ ድርጅት ያቋቁማሉ ። ሦስተኛ ሥራ ሲያጡ ሕዝቡን እየበዘበዙ ወዛቸውን ሳያፈሱ በሰው ወዝ ለመኖር ስለሚፈልጉ የሃይማኖት ድርጅት ይመሠርታሉ የሁሉም የመስበኪያ መንገድ ግን አንድ ነው ። እሱም እግዚአብሔር በሕልም ነገረኝ በራእይ ገለፀልኝ ለአንድነት የቆመች ድርጅት እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን የእኛ ናት በእኛ ቤተ ክርስቲያን ያላመኑና ያልተጠመቁ አባል ሆነው ያልተመዘገቡ ሁሉ ወደ ሲኦል ከመግባት በስተቀር ወደ ገነት ወደ መንግሥተ ሰማያት የመግባት እድል የላቸውም መጾምም ከነገር እንጂ ከእህል ውኃ መጾም አያስፈልግም እያሉ ያስተምራሉ ። በጣም የሚያሳዝነው ግን አምላካችን እግዚአብሔር ምግባር ለሠሩና በሃይማኖት ለፀኑ ክርስቲያኖች መኖሪያ እንዲሆኑ የሠራቸውን (ያዘጋጃቸውን) ገነትናመንግሥተ ሰማያትን በእነሱ ቁጥጥር ሥር አድርገውየእኛ ተከታዮች ይገባሉ የሌሎች ተከታዮች አይገቡም እያሉ የድፍረት ቃል መናገራቸው ነው ። በመሆኑም ይህ ዓይነቱ የሃይማኖት ብዛት የፈጠረው ውድድር በሐብት ሳይወሰን መንፈሳዊ ውድድርምበሰዎች አእምሮ እንክርዳድ እየዘራ ሕዝቡን ከሕዝቡ አንድነት ይልቅ መለያየትን ከዚሁ ጋር ጭቅጭቅና ንትርክን አፍርቶ የሰላም እረፍት አጥቶ ፈሪና ተጠራጣሪ እንዲሆን አደረገው እንጂ አልጠቀመውም ።

ይህም አባባላቸው እንደ ድንበር ዘለል ኩባንያ ስላስቈጠራቸው ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር እንዲለዩ አድርጓቸዋል ። እንግዲህ ይህንን የጻፍነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች የሆኑ ሁሉ በእነዚህ ስብከት ሳይታለሉና ሳይሞኙ በምግባራቸውና በእምነታቸው ፀንተው እንዲኖሩና የተናገሩት ሁሉ እውነት እንዳይመስላቸው ሐሰተኞች መሆናቸውን እንዲያውቅ ለመገፋፋት ነው ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

# የመምህር እሸቱ ወ/ሐና አጭር የሕይወት ታሪክ

መምህር እሸቱ ወ/ሐና ከአቶ ወልደ ሐና ጥላሁንና ከወ/ሮ ቸኮለች ሳሴ በሸዋ ክፍለ ሀገር በእነዋሪ ወረዳ በጅሩ አካባቢ በ፲፰፻፹፰ ዓ/ም ተወለዱ ዕድሜአቸው ለትምህርት በደረሰ ጊዜ በተወለዱበት አካባቢ ከፊደል እስከ ዳዊት ከተማሩ በኋላ ለግብረ ዲቁና የሚያበቃቸውን ትምህርት ተምረው መዓርገ ዲቁና ከብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ግብጻዊው ተቀብለው ቤ/ክርስቲያንን በማገልገል ላይ እንዳሉ በ፲፰፻፺፮ ዓ/ም (በ፲፬ ዓመታቸው) ወደ ሐረር ሄዱ በሐረር ከተማ ከመምህር ገብረ እግዚአብሔር ዘንድ ጾዋትወ ዜማ ጾመ ድጓ ፣ ድጓ ከነጓዙ አጠናቅቀው ተማሩ ።


መምህር እሸቱ ወ/ሐና እኒህ ነበሩ

ከዚያም ወደ ጎጃም ክ/ሀገር ሄደው ከመሪጌታ ጌቴ ዘንድ ቅኔ ከነ አገባቡ ለአምስት ዓመታት ያህል ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል የቅኔ አገባቦችም አውቀዋል ቀጥለውም ወደ ጎንደር ክፍለ ሀገር በመሄድ ዙር አባ ከተባለው ቦታ ዝማሬ መዋሥዕት ለሦስት ዓመት ተምረው ተመርቀዋል።

እንደ ገና ወደ ሐረርጌ ክፍለ ሀገር ተመልሰው ከመምህር ሐዲስ ወ/ጻድቅ ዘንድ የብሉያትንና የሐዲሳትን ትርጓሜ አጠናቅቀው ከ[illegible]





www.ethiopianorthodox.org

አውቀዋል እንዲሁም ከአለቃ ለማ ኃይሌ ዘንድ የሐዲሳትን ትርጓሜ ከልሰው በመማር ተመርቀዋል ። በተጨማሪም አሥራ አራቱን ቅዜማ (መዝገበ ቅዳሴ) አጠናቅቀው ተምረዋል በትርፍ ጊዜ አቸው ዘመናዊ ትምህርት እስከ ሰባተኛ ክፍል ተምረዋል ።

መምህር እሸቴ ወ/ሐና በ፲፱፻፳ ዓ/ም በሐረር ከተማ በጥምቀተ ባሕር ቅ/ሚካኤል ቤ/ክርስቲያን ትክለኛ የነበሩትን የመምሬ ሲደልል ጥላሁንን ልጅ ወ/ት ጥሩነሽ ሲደልልን በተክሊልና በቊርባን አግብተው አራት ሴቶችንና አራት ወንዶች ልጆችን አፍርተው ከነዚህ ልጆቻቸው አብራክ የተገኙት አሥራ ስድስት የልጅ ልጆች ለማየት በቅተዋል «መምህር እሸቴ ወልደ ሐና በሐረር አደሬ ጢቆ መካነ ሥላሴ ደብር ከወጣትነት ዘመናቸው ጀምሮ በግብረ ዲቁና በሊቀ ዲቁና ለ፴ ዓመታት ያህል አገልግለዋል ከዚያም በራስመኰንን ት/ቤት በግብረገብ መምህርነት ተቀጥረው ለሃያ አምስት ዓመታት ያህል በትጋትና በንቃት አገልግለዋል እንዲሁም በአደሬ ጢቆ መካነ ሥላሴ ደብር በአስተዳዳሪነት ለ፴ዓመታት ሠርተዋል ።

በአገልግሎት ዘመናቸው በአደረጉት የሥራ ጥራትና ታታሪነት በትምህርትና ስነ ጥበብ ሚኒስትር ም/ሚኒስትር እጅ ልዩ ሽልማትና የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል።

ከዚህም ሌላ የሕፃናትን አእምሮ በሞራል በዲሲፕሊን በማነፃቸው ከራስ መኰንን ት/ቤት ዳሬክተር የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል።

መምህር እሸቴ ወ/ሐና በ፲፱፻፷፩ ዓ/ም መዓርገ ቅስናን ከብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ግብፃዊ ተቀብለዋል ። እኚህ ታላቅ አባት ብዙ ምእመናን ግብረ ገብነታቸውንና ትምህርታቸውን በማየት ወደ ቤታቸው በመምጣት እንዲያስመተሩአቸውና መምህረ ንስሐም እንዲሆኑአቸው ይለምኑአቸው ነበር ።

መምህር እሸቴ ወ/ሐና ከመምህርነት ሥራቸው ጋር በመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ብቻ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ለ፴፱ ዓመታት ያህል በትንነትና በታማኝነት ሰራ እገልግሎት አበርክተዋል ፡ ይልቁንም ሲገለገሉበት የነበረው ድጓ ፡ ጾመ ድጓ ለዚሁ ለሚወዱት ደብር በመስጠታቸው ሊታወቁ ፡ ፡ [illegible] ምእመናንና ምእመናቱ [illegible] [illegible] ትርጓሜ መጻሕፍት [illegible] ጻሕፍት ሐዲሳትን [illegible] ያተ ክርስቲያናት [illegible]

እግዚአብሔር [illegible] ችን ሕዳም «እ እዳም መሬት አንተ ወተገብሽ ውስተ መሬት [illegible] ሰጠው ውሳኔ መሠረት [illegible] ሰው ዘር ዘር [illegible] ፊት ምንም ቢሆን አይቀርምና መምህር እሸቴ ወ/ሐና በ፷፰ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

መምህር እሸቴ ወ/ሐና መላ ዘመናቸው በምግባረ ሠናይ ያሸበረቁ በመሆናቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ የድካማቸውንና የአገልግሎታቸውን ዋጋ ስለሚቀበሉ ሕያው እንጂ ሙት አይደሉም ምክንያቱም ቅዱስ መጽሐፍ የጻድቅ ሰው ሞት በእግዚአብሔር ፊት ክቡር ነው የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ማስታወስ እርግጡን ያስረዳናልና ። መምህር እሸቴ ወልደ ሐና በእርግናቸው አንፃር ቤተ ሰዎቻቸው እነ ሡኝ እቅኑኝ ጡሩኝ እርዱኝ ብለው ሳያስቸግሩ ከዚህ ዓለም ተለይተዋል ።

መምህር እሸቴ ወ/ሐና የሐረር ከተማ ሊታወቁት መምህራንና ምእመናን እንዲሁም በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ የከተማው ነዋሪዎች ወዳጅ ዘመድ በተገኘበት ሥርዓተ ቀብራቸው በዚያው በሚወዱት ደብር ተፈጽሞአል ። ስለዚህ በሕይወታቸው ጊዜ በደስታም በኀዘንም ሳል ተለዩአቸው ባለቤታቸውና ለመላው ቤተ ሰዎቻቸው መጽናናቱን እንዲሰጥልን የልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን እያልን እስከ [illegible] እንሰናበታቸዋለን ።

[illegible] መካነ ሥላሴ ቤ/ክርስቲያን [illegible] ጉባኤ ጽ/ቤት

## የጤና ዓምባ ዕድር [illegible]
## ቅድሳት ስጦ[illegible]

በከፍተኛ ፲፩ ቀበሌ ፲፬ በኃይለ መለኮት መንገድ የሚገኘው የጤና ዓምባ የሕዝብ መረዳጃ ዕድር በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ክልል ለሚገኘው የመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስና ቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክርስቲያን ሊቃና ዘገሊላ በዓልና ለታቦቱ ሕጉ ማክበሪያ የሚሆን የገንዘብና የንዋየ ቅድሳት ስጦታ ማበርከቱን የዕድሩ ዳኛች አቶ አሥራት [illegible] በሌና ሻምበል ባሻ ፍትሕ [illegible] ቸርነት ገለጹ ።

ዕድሩ ያበረከተው ስጦታና ያደረገው አስተዋጽኦ ዳኞቹ ሲያብራሩና የጽሑፍ ማስረጃ በማቅረብ ሲያስረዱ ዕድሩ

፩ኛ/ በየዓመቱ ለሚደረገው የቃና ዘገሊላ ክብረ በዓል ከ፲፱፻፸፫ ዓ/ም ጀምሮ እስከ ፲፱፻፹፪ ዓ/ም ድረስ ለመስተንግዶ ይሆን ዘንድ በጥሬ ገንዘብ ብር ፫፻፳፬ (ሦስት መቶ ሃያ ዘጠኝ ብር) ዓባላቱ አስተዋጽኦ እያደረጉ በዕድሩ ኃላፊዎች አማካይነት ገንዘቡ ተሰጥቷል ።

፪ኛ/ ይህ ዕድሩ በ፲፱፻፹ ዓ/ም በብር ፫፻፬ (ሦስት መቶ አራት ብር ከሰማንያ ሣንቲም) የፈጀ አሥራ ሁለት መቋሚያዎች ከነዘንጉ ገዝቶ ለደብሩ ማስረከቡን የመንበረ ልዑል ማርቆስና የቅዱስ ሚካኤል ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት የተረከበበት የገቢ ደረሰኝ በዝርዝር አቅርበው አሳይተውናል ።

፫ኛ/ በ፲፱፻፹፫ ዓ/ም በብር ፩፻፺፬ (አንድ መቶ ዘጠና አራት ብር) የተገዛ የናስ ጻናጽል ከነማኀደሩ የጤና ዓምባ ዕድር ከላይ ለተጠቀሰው ደብር በዝርዝር ገቢ ማድረጉን ዳኛው አቶ አሥራት ታችበሌና ም/ዳኛው ሻምበል ባሻ ፍትሕ አወቅ ቸርነት ያቀረቡት ደረሰኝ ይገልጻል ።

፬ኛ/ በ፲፱፻፹፪ ዓ/ም ደግሞ ለታቦተ ቅዱስ ሚካኤል ማክበሪያ ይውሉ ዘንድ ከወርቀ ዘቦ የተሠሩ ሁለት መጐናጸፊያዎች በዕድሩ ስም መስጠቱን ከዕድሩ የተገኘውና በማስረጃ የተደገፈ ዘገባ ያመለክታል ። ይህ ሁሉ በገንዘብ ሲተመን ብር፩፻፲፬ ከዜሮ ፭ሳንቲም (አንድ ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ አራት ብር ከዜሮ አምስት ሳንቲም) መሆኑንም አክሎ በማብራራት አስረድቷል ።

ቤተ ክርስቲያን ለሕዝብ ከተቆጠረችበት ጊዜ ጀምሮ ክርስቲያኑ ሕዝብ ስለ ቤተ ክርስቲያኑ ያለው ፍቅር የቱን ያህል እንደሆነ ከዚሁ ለመረዳት ይቻላል እንደ ጤና ዓምባ የመሳሰሉት ታላላቅ ዕድሮች ቤ/ክርስቲያናቸውን በከፍተኛ ንቃትና ትጋት ከመንከባከባቸውም በላይ የሚያስፈልጋትንም ሁሉ እያሟሉ መንፈሳዊ አገልግሎቱ በተሳካ ሁኔታ እየተካሄደ እንዲሚገኝ የተረጋገጠ ነው ።

የመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስና ቅ/ሚካኤል ቤ/ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ አባለውለታውና [illegible] [illegible] የጤና ዓምባ ዕድር [illegible] [illegible] [illegible] ዕድራችሁ [illegible] ቅና የቃና ዘገሊላን በዓል ንግሥ [illegible] ማክበሪያ [illegible] ስለተንግዶ ባደረጋችሁ የገንዘብ ርዳታና የመንፈሳዊ አገልግሎት መፈጸሚያዎች የቱን ያህል እንደሆነ ትብብራችሁና በዓሉን በላቀ ክብር በማንገሣችሁ እጅግ ታላቅ ክብርና ደስታ ይሰማናል »ካለ በኋላ «ላደረጋችሁልን ርዳታና ልባዊ ትብብር በሐዋርያው በቅዱስ ማርቆስና በመልአኩ በቅዱስ ሚካኤል ስም እግዚአብሔር ዋጋችሁን ይከፍላችሁ ዘንድ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዘወትር በጸሎት አትለያችሁም» የሚል ይገኝበታል ።



የጤና አምባ ዕድር ሥራ አመራር አባላት እነዚህ ናቸው

እንዲሁም በ፲፱ ፡ ፲፱፻፸፫ ዓ/ም በተጻፈ የምስጋና ደብዳቤ አድራሻው ለዕድሩ ሆኖ «ይህ ቤ/ክርስቲያን ከሌሎች አድባራት በዚ. ረገድ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል እያልን በየጊዜው ብንናገርም እደራችሁን በመሳሰሉ የቤ/ክርስቲያኑን ችግር እንደራሱ አድርጎ የሚመለከትና ለችግሩ መፍትሔ የሚሆ በአካባቢያችን ስናገኝ [illegible] እንኩራራለንም ።

ምንም እንኳ የቤ/ክርስቲያኑን ችግር አስመልክተን ከ፲፱፻፸፭ ዓ/ም





www.ethiopianorthodox.org

ለጥምቀትእና ቃና ዘገሊላ በዓል ዕለት እንግዳ ማስተናገጃ ይሆን ዘንድ ቀደም ባለው ጊዜ ርዳታ ብን ጠይቅም ለቤ/ክርስቲያንዋ የሚያ ስፈልጓት የመንፈሳዊ አገልግሎት መሣሪያዎች ዕጥረት መኖሩን በመ ረዳት ይህን የመሰለ ውድ ስጦታ ማበርከታችሁ በነፍሳችሁና በሥጋ ችሁ እንደምትጠቀሙበት የማያጠ ራጥር ሐቅ ነው ።

ይህን ቅጥሩ ፲፱ የሆነ የመንፈሳዊ አገልግሎት መሣሪያ በኃይለ መለ ኮት መንገድ የሚገኘው የጤናዓም ባ ዕድርና የስጦታው ተቀባይ መን በረ ልዑል ቅ/ማርቆስ ቤ/ክርስቲ ያን ስም ያለበትን ከነሐስ የተሠራ ጻናጽል ከነማስቀመጫው ሳጥን ሚያዝያ፩ቀን ፲፱፻፸፰ ዓ/ም የዕድሩ ኃላፊዎችና ዓባላት እንዲሁም የደ ብሩ ሰ/ጉ/አባላትና ማኅበረ ካህናት በተገኙበት ለቤ/ክርስቲያኑ የተደ ረገውን ስጦታ በምስጋናና በጸሎት ተቀብለናል» ካለ በኋላ «እንደ እውነቱ ከሆነ እስከ ዛሬ ድረስ ከብረ በዓላት በመጡ ቍጥር መገ ልገያ መሣሪያዎች እንደ ጸናጽልና ሌሎችም የመንፈሳዊ አገልግሎት መሣሪያዎች እጥረት ስለነበረ ከአቅራቢያ ቤ/ክርስቲያናችን እየ ተዋስን እንጠቀም ነበር ። አሁን ግን ለእግዚአብሔር ክብር ምስ ጋና ይግባውና በእናንተ ላይ አድሮ ይህን የመሰለ ስጦታ እንድታበረ ክቱ በቅዱስ መንፈሱ ስለቀሰቀሳ ችሁ ከጸናጽልና ከመሳሰሉት መን ፈሳዊ መሣሪያዎች መዋስ ድነናል

በዛሬ የኑሮ ውድነት የዕድሩ ዓባ ላት ከቤተሰዎቻቸው አፍ ነጥለው ለቅድስት ቤ/ክርስቲያን በመስጠ ታቸው እናንተም ይህ የተቀደሰ ስጦታ ገዝታችሁ በመስጠታችሁ በቤተ ክርስቲያን ምን ጊዜም የማ ይረሳና ሲታወስ የሚኖር ትልቅ ውለታ ነው ፤ በዚህም አጋጣሚ ከዚህ በፊት ስታደርጉልን የነበረው ድጋፍ የማይረሳ በመሆኑ ምሥጋና ችንን ልናቀርብ እንወዳለን ርዳታ ችሁና ትብብራችሁም ለወደፊቱ እንደማይለየን ተስፋ እናደርጋለን በማለት ደብሩ ዕድሩን አመስግኖ በመጨረሻም ከመጽሐፍ ቅዱስ ምርጥ ክፍል በመፈለግ ።

«በበጋ የሚያከማች ልጅ አስተ
ዋይ ነው
በመከር ጊዜየሚተኛ ግን እርሱ
ራሱን ያስነውራል
በረከት በጻድቅ ራስ ላይ ነው
የኃጥአንን አፍ ግን ግፍ ይከድ
ድነዋል
የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው
የኃጥአን ስም ግን ይጠፋል »

በማለት የዕድሩን ምስጋና ሀ/ጠቢቡ ሰሎሞን የተነገረውን የአስተዋዩት ምክር ሰጥቶ የዕድሩ አባሎች ስም እግዚአብሔር በሰማያዊ መዝገቡ እንዲመዘግብላቸው በጸሎት የሚ ለምኑ መሆናቸውን አረጋገጠውላቸ ዋል ።

እኛም እዚሁ ላይ ልናክልበት የምንፈልገው ቁም ነገር ቢኖር ቤተ ክርስቲያን የሕዝበ ክርስቲያን አካል መሆንዋን የጤናዓምባ ዕድር ከመገንዘቡ የተነሣ የመንበረ ልዑል ቅዱስ ሚካኤልን ቤ/ክርስቲ ያን ለመርዳት ታጥቆ በመነሣቱ ለሌሎች ዕድሮችም መልካም አርአ ያና ምሳሌ እንደ ሚሆን እየተማመ ንን በዚህ አጋጣሚ ጊዜ አንተ የምትተኛ ንቃ ከእንቅልፍህም የም ትነሣበት ጊዜ አሁን ነው ብሎ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ጻፈው ለመሥራትም ለመስጠትም አሁን ነውና እንደ መንበረ ልዑል ያሉት አብያተ ክርስቲያናት በገቢ በኩል ብዙ ችግር ስለሚኖርባቸው መርዳቱና ማበረታታቱ የተቀደሰ ተግባር መሆኑን ተገንዝበው እጃ ቸውን እንዲዘረጉ የሚሰጥ በልግ ሥና ይስጥ ያለውን የጠቢቡን ምክር እንዲከተሉ ይገባል እንላለን

## ክርስቲያናዊ ሕይወት

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለሦስት ሺህ ዘመናት በነጻነቷዋ ታፍራና ተከ ብራ ኑራለች ሲንል በነዚህ ብዙ ሺህ ዓመታት በየዘመናቱ በኢት ዮጵያ ኖረው ያለፉ አባቶቻችን አቋማቸው (ኗኗማቸው) እንዴት ነበር ? ዘመናቸውስ በምን ዓይ ነት ሁኔታ ኢሳለፉት ? ባሳለፉ ኣቸው ዘመናቸስ ከትውልድ ወደ ትውልድ እያስተላለፉ እስከኛ ያደ ረሱአቸው ባሕሎች ፤ ወጎችና ቅር ሶች ምን ምን ናቸው ? ብለን መመ ርመርና መጠየቅ ይኖርብናል ።

ጥያቄአችን በነዚህ ብናተኩር የም ናገኘው ማስረጃና መልስ ጠቃሚ እንደሚሆን ይገመታል ።

በተለይም በዓለም ኅልቶና ተስ ፋፍቶ ሲነገር የኖረውና የሚኖረው የአባቶቻችን ታሪክ ሃይማኖተ ጽኑ ዎች ፤ ጀግኖች ፣ ኩሩዎች ፣ ደፋ ሮች ፣ ሀገርንና ወገንን አፍቃሪ ዎች ናቸው የሚል ነው ፤ እንዲሁም የበጎ (የትሩፋት) ሥራ ሠሪዎች ናቸው የሚለው ስመ ጥር ቀዳሚ ዜናቸው የኃላ ታሪካቸው ሆኖ ይታ ያል ። ሌላው ታሪካቸው እንግዳ መቀበልን ፣ መጋበዝን ፣ ወገንና ሀገርን ማክበርና መውደድን የመ ሳሰሉት ሁሉ ከጥንታውያን አባ ቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ እስከኛ የደረሱ የተቀደሱ ሥራዎቻቸው ናቸው ።

በዚህ አኳያ አባቶቻችን የሚያ ደርጉአቸው (የሚያሳዩአቸው) ሌሎ ች ባሕርያት ነበሩአቸው ። ይኸ ውም በንቀት ፣ በማቃለልና በማ ታለል የሚያዩአቸው ፣ በድፍረት የሀገራችንን ዳር ድንበር ጥሰው ለመግባትና ወደ ሀገራችን ገብተው የቅኝ ገዥነትን ለማስፈን ላዩ ማር ውስጡ እሬት እያደረጉ ሊያሞኙ አቸው ያሰቡ የውጭ ዜጎች ሲያ ጋጥማቸው እንደግሥ ላና እንደ አራስ ነብር ጠላቶቻቸውን አሳፍ ረውና አሳድደው ያባርሩአቸው እን ደነበሩና ከቶ ውንም ጸበለ እግራ ቸው (የእግራቸውን ትቢያ) እንኳ ሳይቀር አራግፈው ይሰዱአቸው እንደነበር በታሪክ ተረጋግጦአል ።

ይሁን እንጂ ጠላቶቻችን እንደ ምንም ብለው ወደ ሀገራችን እየ ገቡ ዘርተውት የሄዱ የማለያያና የኑፋቄ አዝመራ ባሁኑ ጊዜ እየተ ስፋፋና ብዙ ፍሬ እያፈራ በመም ጣቱ አዋቂዎቹን ያሳዝናቸዋል ሞኞ ቹን ግን ሥልጣኔ ስለሚመስ ላቸው ያስደስታቸዋል ፤ ስለዚህ ብዙ የማናውቃቸው ባሕሎች ወጎችና ሥርዓቶች በየጊዜው በኅ ብረተ ሰቡ መካከል እየተከሡቱ ይታያሉ፤በሀገራችን ታይቶና ተሰ ምቶ የማይታወቅ በንግግር ፣ በጽ ሑፍ ለመግለጽ የማይቻል ርካሽና አስነዋሪ ነገር ይታያል፣ ይፈጸማል። ይህም ደግሞ ከማንም ኢትዮጵያዊ ዓይነ ሕሊና የተሠወረ አይደለም የዚህ ሁሉ ውጤት የተለያዩ በሽታዎች ፣ የኑሮ ቀውሶችና ችግ ሮች የመሳሰሉት ናቸው ፤ ከሁሉ የሚያሳዝነው መድኃኒት የለሽ ቀ ሳፊ በሽታ መሠረቱ ይህ እንደሆነ የታመነ ነው ።

ምናልባት አንዳንድ ሰዎች የበ ሽታው መንስኤ (ምንጭ) በአንድ አቅጣጫ ይመለከቱት ይሆናል እ ንደ እኔ አስተሳሰብ ከሆነ ግን ኅብረተ ሰቡ ለዚህ በሽታ መከ ሰት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደ ረገለት እገምታለሁ ። ይኸውም አንዱና ትልቁ ነገር እግዚአብሔርን በመርሳቱ ነው ፤ ሁለተኛው ደግሞ በጥጋቡ ያመጣው ነው ለማለትይቻ ላል ፤ አባቶቻችን ከተራበው ለጠገ በው አዝናለሁ ብለው የተረቱት ያለ ምክንያት አይደለምና ፤ ከዚ ህም ሌላ ካልጠገቡ አይዘሉ ካልዘለሉ አይሰበሩ የሚለው የአ በው ምሳሌያዊ ንግግር እዚህ ላይ ቢጠቀስ እንደሚስማማው እተማ መንበታለሁ ። ሦስተኛው ምክ ንያት ደግሞ ይህን ዓለም ከመ ፍራት የተነሣ ነው ብዬ አስባለሁ ብዙ ለመተንተን ሲቻል ነገር ግን በነዚህ ብቻ ሀሳቤን ለመግ ታት እሻለሁ፣ ምክንያቱም እነዚህ ሦስት ዐርእስተ ጉዳዮች እያንዳን ዳቸው ስንተነትናቸው ብዙ ጊዜ ስለሚወስዱብን ነው ።

እግዚአብሔር እንዴት ተረሳ ፣ የረሳውስ ማነው ? የሚል ጠያቂ ይኖር ይሆናል መጠየቅም ተገቢ ነው፤መልሱ ግን ቀላል ነው በዘመ ናችን በአማንያንና በኢአማንያን መካከል እንደምናየው ከሆነ የእ ምነት ልዩነት ያለ አልመሰለኝም ፤ ምን ለማለት ፈልጌ ነው? ይኸውም እምነት የለኝም ያለውንና እምነት አለኝ የሚለውን በተግባር ስናነጻጽ ረው እነዚህ ሁለቱ ወገኖች የአፍ ልዩነት ይኖራቸው እንደሆን እንጂ በግብር አንድ ሆነው በመገኘታ ቸው ነው ። ታላቁ መጽሐፍ «አል ቦ ዘይገብራ ለሠናይት ወኢአሐዱ» መልካም ነገርን የሚሠራት ፣ የሚ ከተላት የሚፈጽማት የለም አንድ ስንኳ የለም» ይላል ። ይህ ቃል እንዲሁ ለጥዛ ለፌዛዛ የተነገረ ሳይሆን መንፈስ እግዚአብሔር ያደ ረበት ሰው የሰዎችን ሁኔታ አይ ቶና ተመልክቶ ፋይዳ እጥቶበት የተናገረው ነው ።

ምናልባት አባባሌን የሚቃወም ሰው ይኖር ይሆናል ምን ማለቱ ነው! እግዚአብሔር አለ የሚለ ውንና እግዚአብሔር የለም የሚ ለውን እንዴት አንድ ነው ይላል! እምነታችንን የሚቃወም ጽሑፍ፣ (ንግግር) ነው እንዲህ መሆን የለ በትም እያለ ለመንቀፍም ለመገዝ ለፍም የሚሞክር ይኖራል» ይሁን ነቃፊም ተነቃፊም ያለ የነበረ ነው ሐቁ ግን እንዲህ አይደለም ። ለመሆኑ እግዚአብሔር ማነው፣ የሰጠው ትእዛዝስ ምን የሚል ነው ? ትእዛዛቱን ካልፈጸምንስ ክርስቲያ ናዊ ሕይወታችን ምን ያህል ክብር ያገኛል ? ብለን ራሳችን በራሳ ችን መጠየቅ ይገባናል በቅዱስ ወን ጌል «መልካም የሆነ አንድ ነው ወደ ሕይወት መግባት ገብተህ በሕይወት ለመኖር ብትወድ ብት ፈልግ ትእዛዛቱን ጠብቅ»የሚል ተጽፎአል ፤ ሕይወት ወዳለበት ለመግባት ገብቶም በሕይወት ለመ ኖር የማይወድ ትእዛዛትን አይ ጠብቅም ትእዛዛትን የማይጠብቅ ሰው ደግሞ ሕይወትን ለማግኘት እንደማይችል ከዚህ በላይ ተጠ ቅሶአል ።

ትእዛዛቱ ምን የሚሉ ናቸው ? ፩ኛ እግዚአብሔር አምላክህን በፍ ጹም ኃይልህ ውደድ ፤ሁለተኛዪቱና እርሷን የምትመስለው ደግሞ አባ ትና እናትህን ወንድምና እህትህን አክብር የሚልቅሕን (በዕድሜ የሚ በልጥህን /የሚያንስህን ጎረቤትህን መሰልህን በአጠቃላይ ጠላትህም ወዳጅህም ሁሉ በአንድ ዓይነት አመለካከት በአንድ ዓይነት አስ ተያየት ውደድ አሥርቱ ትእዛዛተ እግዚአብሔር በነዚህ ሁለት ተራ ቍጥሮች ተጠቃልለዋል ይላል ።

ታዲያ በእውነት እግዚአብሔር አምላኩን በፍጹም ነፍሱ፣ በፍጹም ኃይሉ የሚወድ አለ? በቃል እም ነት አለኝ የሚል ሁሉ እምን እግዚአብሔርን እወደዋለሁ እንደ ሚል አምናለሁ ነገር ግን ሐሰት ነው፤ይኸውም እንዳንዱ ወደ ጠን ቋይ ፣ ወደ ቃልቻ፣ ወደ መጽሐፍ ገላጭ፣ ወደ ዛር ወላጅ፣ ወደ ስር ማሽ ቅጠል በጣሽ ወደዚህ ሁሉ ባይሄድ እንኳ ቢታመም ቢያጣ ፤ ቢነጣ ፣ ቢቸገር ፣ ቢደኸይ እግዚአ ብሔር ካለ ለምን ድሐ አደረገኝ ፣ ለምን እንደነ እገሌ ባለጸጋ አያ ደርገኝም ነበር? እያለ በኑፋቄ (በጥ ርጥር) ላይ ወድቆ እንደሚኖር እ ሙን ነው ያለውም ቢሆን በቃኝን አያውቅም እንዲያውም እንዳንዱ





www.ethiopianorthodox.org

ቹ ቢያገኙ ከቤተ እግዚአብሔር የሚርቁ፣ጊዜ እቸውን በዋዛ ፈዛዛ የሚያሳልፉ ሆነው ይታያሉ ለተቸገረ ወንድማቸው ላጣ ለነጣ ወገናቸው አያዝኑም አይራሩም ሌሎቹ ደግሞ ከወንድሞቻቸው ከእህቶቻቸው ተጣልተው ይቅርታ የማያደርጉ ናቸው እንዲያውም እቤተ ክርስቲያን መጥተው እባክህ አምላኬ ሆይ ዕገሌ እንዲህ እንዲህ አድርጎ በድሎኛል ዛሬ ጀምበሪቱ ሳትጠልቅ የእሱን ነገር ካላሳየኸኝ ፈጽሞ መለስ ብዬ ከበርህ አልደርስም ፤ ሀብቱን፣ጥሪቱን፣ቤቱን፣ ንብረቱን፣ሚሽቱን፣ልጆቹንም፣ራሱንም፣ድራሹን፣ካጠፋህልኝ፣በዚህ ወር ውስጥ እኗኗሩን፣ ስመ ዝክሩን እንዳልነበረ ካደረግህልኝ ግን የዛሬ ወር የወርቅ ጃንጥላ ፣ አልባሳት ፣ ንዋየ ቅድሳት ወዘተ --- ይዤልህ እመጣለሁ የሚሉም አሉ ።

ታዲያ እነዚህ ሁሉ የሚጠሩ በአማኝ ደረጃ አይደለም? ክርስቲያን ነህ? ተብሎ ሲጠየቅ መልሱ አዎ እንዴታ ! ! የሚል አለ ። ክርስቲያናዊ ተግባር ትፈጽማለህ? ሲሉት ግን እንደቢታንያ በለስ ቅጠል ብቻ ነኝ ከሚል በስተቀር ፍሬ ትሩፋት የለውም እንግዲያስ እግዚአብሔር እንዳለማ አጋንንትም ያምኑ የለ? አሁንም ለዚሁ ጥቅስ ዋቢ ያችን ታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ ነው «እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ ፣ መልካም ታደርጋለህ ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል አንተ ከንቱ ሰው እምነት ከሥራ ከተለየ ወይም ሥራ የሌለው እምነት የሞተ እንደሆነ አታውቅምን?» ይላል ። በዚህ ጥቅስ እምነትና መልካም ምግባር አንድ እንደሆኑ እንረዳለን ከሁለቱ አንዱን ነጥሎ ለመያዝ ወይም ደግሞ ከሁለቱ በአንዱ እጸድቃለሁ ብሎ ማመን አይቻልም ። ስም ያለፈትል ፤ፈትል ያለ ስም ተለያይተው ብርሃን ለመስጠት እንደማይችሉ ለማንም ግልጽ ነው ።

ሐዋርያው ምን ማለቱ ነው? እግዚአብሔር ብቻ በአፌ ባምን እጸድቃለሁ ሌላ ምግባር (መልካም ሥራ) ማለት አባትና እናትን ወንድምንና እህትን በአጠቃላይ መሰል የሆነው ሰውን ግን አልወድም የሚል እጸድቃለሁ አይበል ነው ፤ እግዚአብሔር ማነው? ለሚለው ጥያቄ እግዚአብሔር ፍቅር ነው ወንጌላዊው ዮሐንስ «እኛም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አውቀናል አምነን ማል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል» ሲል ያስገነዝባል ። ታዲያ ሰዎች እምነት አለን የሚሉ ሁሉ ፍቅር ማለት እግዚአብሔር ነው ብሎ አል በልባቸው ፍቅርን ጠልተው በአፋቸው ብቻ ፍቅርን እንወዳለን እንከተላለን ሲሉ ሐቁ እምን ላይ ነው? አሁንም ወንጌላዊው «ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው ያየውን ወንድሙን የማይወድ (ሳይወድ) ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወድ እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርንም ደግሞ የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ ተሰጠችን» ይላል ።

ይህ የጥቅሱ መጨረሻ ነው እንግዲህ ከዚህ በላይ እንደሰማነው ወይም እንዳነበብነው ፍጹማን እማንያን የሚባሉት ይህ ትእዛዝና ሕግ የሚከተሉትና የሚፈጽሙት ናቸው ከፍ ብለን እንደተናገርነው በአፍ ብቻ አማኝ በተግባር ግን ፈጽሞ ምልክት እንኳ የሌለን ከሆነ ክርስቲያን ነኝ ወይም እምነተኛ ነኝ ብሎ ማንም ሰው ሊጸድቅ እንደማይችል መገንዘብ ብልህነት ነው እለዚያ «ከመረቁ አውጡልኝ ከሥጋው ጾመኛ ነኝ» ተብሎ የተነገረው የአበው ተረት በኛ ላይ በቂ ሥፍራ ያገኛል ፤ ምናልባት በዚህ — ዓለም እያታለልን ወይም መስለን ብንኖር እንኳ እምነታችን የሚፈተንበት ወቅት እንዳለ መዘንጋት አይገባም ።

ሦስተኛው የጽሑፋችን ሀሳብ ሰዎች ዓለምን ከመፍራት የተነሣ ከጋብቻ ዓለም ስለሚሸሹ ለመድኃኒት የለሽ በሽታ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል ፤ ታላቁ መጽሐፍ እንደሚነግረን ሰዎች በመጀመሪያ ወንድና ሴት ሆነው እንደተፈጠሩ ነው። ከእነዚህ የተገኙ ልጆቻቸው በጋብቻ ዓለም ተሳስረው ወልደው ከብደው መልካም ዜጋ አፍርተው በዓለም እንዲኖሩ ምድርንም እንዲሞሉአት ሕግ እንደተሠራላቸው መጻሕፍት ይነግሩናል ታዲያ በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተገኘው ትውልድ ሴትዋ እርግዛ ፣ ወልዳ ፣ አጥብታ ማሳደጉን በመጥላት ፣ ወንዱም ሴት አግብቶ የሴት ልብስ ጫማ ልዩ ልዩ ጌጣጌጥ ባጠቃላይ የቤት ጣጣ የሆነውን ሁሉ አምጣ እንደሚባል አውቆ በመሰጋት ፣ ሲወልዱ ለልጁ ማሳደጊያ ፣ ልብስ ፣ ትምህርት ቤት ፣ ደብተር ፣ እርሳስ መግዛቱን ስላሰቀቀው ለብቻው መኖርን መረጠ ፤ ይሁንና ሴቱም ወንዱም ለየብቻቸው በድንግልና ጸንተው ከግንኙነት ርቀው ነው የሚኖሩት? የሚል ጥያቄ ያስከትላል ይህም መልሱ በድንግልና ጸንተው እንደማይኖሩ ራሳቸውም የሚመሰክሩት ነው።ደግሞም ሴትየዋ ፍቅረኛዋ አንድ ነው ።ወንድም እንደዚሁ እንዳይባል አንድነቱን ጠልተው ፡ ተራርቆ መኖርን መርጠው ስለሚኖሩ አባባሉ ማንም አይቀበሉም ምክንያቱም የሰው ባሕርይ ተለዋዋጭ ስለሆነ ሴትዋ ከምታየው ካማረት ወንድ ጋር፡ወንዱም እንደዚሁ ነጋም ጠባም ደስ ካላቸው ሰው ጋር ፍትወተ ሥጋቸውን እርከተው ፣ ኑሮአቸውን የሚገፉት በዚሁ እንደ እንስሳ ድብልቅልቅ በሆነ ኑሮ ስለሆነ ንጽሕና ይጠበቃል እንዳይባል ፍጹም ሐሰት ነው ለማለት ያስደፍራል።ታድያ በዚህ ኑሮ ያሉት ሰዎች ወንደላጤዎች ሴተ ላጤዎች ሁሉቹም እንኳ ባይሆኑ ለበሽታው ምንጮች ናቸው ቢባል ከእውነት የራቀ ስላልሆነ ምክንያቶች ሁሉ



በየአቅጣጫው ተጠራቅመው ለቀሳፊ በሽታው አስተዋጽኦ ሊያደርጉለት ችለዋል በመሆኑም እንዲህ ዓይነቱ አስቃቂ በሽታ በሀገራችን ብሶ ሊከሠት ችሎአል ።

ቤተ ክርስቲያን ይህ ሁሉ እንዳይመጣ አስቀድማ አንድ ወንድ በአንዲት ሴት አንዲት ሴት በአንድ ወንድ ተወስነው መኖር አለባቸው እያለች ጥንቱንም አሁንም አውጃለች ስታውጅም ትኖራለች ። ነገር ግን ቃልዋ እንደቀልድና እንደ ፌዝ ታየ ! ማንዘራሽ ጋብቻ ፣ ማንዘራሽ ኑሮ ፣ ማንዘራሽ ሃይማኖት ተስፋፋ ጋጠ ወጥ ልጆች ተወለዱ ፣ ትሕትና ፣ ፍቅር ፣ ቸርነት ፣ በጎነት ፣ እምነት ፣ ሁሉ ጠፋ ክህደት ፣ ሌብነት ፣ ውሸት ፣ ትጥፈት ፣ መለያየት ፣ መናናቅ ፣ መነቃቀፍ ፣ብቻ ሰፈነ ገነነ ።

ለመሆኑ ይህ ሁሉ የተቀደሰ ባሕልና ወግ ፣ ሥርዓትና እምነት ፣ ይቅር ያለ ማነው? ክፉ ፣ አጥፊ ፣ ጎጂ የሆነ ነገር ሁሉ ይቅር ቢባል መልካም ነበር ፣ ነገር ግን ሀገርንና ወገንን የሚያጠፋ ይስፋፋ ፣ ሀገርንና ወገንን የሚያስለግ ፣ በረከትንና ረድኤትን የሚያስጥ ይጥፋ ፣ ተብሎ የታወጀ ይመስል ተባብሮና ተነባብሮ በመነሣት መልካም ነገር የሆነውን ሁሉ ለማጥፋት መረባረቡ ማንንም አይጠቅምምና በጥንታዊ ብሔራዊ ባሕላችን ብንመራ መልካም ነው እላለሁ ።

ሊ/ ት/ ገ/ ክ/ ኃ/ ማ/

## አስደናቂ ተአምራት በፈለገ ሕይወት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ

በቡልቡላ ፈለገ ሕይወት አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ቤ/ክርስቲያን ሥር በጻድቁ አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ስም የፈለቀው ፀበል ካሁን በፊት በየጊዜው ከጥቅምት ፳ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ/ም እስከ መጋቢት ፳ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ/ም ድረስ በአባታችን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ተራዳኢነት ፲፭ሺ፫፻፹፰ መድረሳቸውን የደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ሕይወት ወልደ ሰንበት እድሐና በበዓሉ ላይ ለተሰበሰቡት ምእመናን በዝርዝር ማስረዳታቸው ሪፓርተራችን ከሥራፍው ተገኝቶ ያጠናቀረው ዘገባ ያመለክታል ።

መጋቢት ፳ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ/ም በአባታችን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ስም በተተከሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በከፍተኛ ድምቀት ሲከበሩ የታመነ ቢሆንም በተለይም በዚሁ ደብር እጅግ በላቀና በደመቀ ሁኔታ ተከብሮ መዋሉን ሪፖርቱ ጨምሮ ገልጾአል ። እያይዞም በበዓሉ ዕለት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ መልካም ፈቃድ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የምዕራብ ጎጃምና የመተከል ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ መገኘታቸውን አመልክቶ ብፁዕነታቸው ከቀኑ አራት ሰዓት ላይ ከሥፍራው ሲደርሱ መልአከ ሕይወት ወ/ሰንበት እድሐና ልብሰ ተክህኖ ከለበሱ ካህናትና ከሰበካ ጉባኤ አባላት እንዲሁም ከደብሩ ሰንበት ት/ቤት መዘምራን በመሆን በክብር ተቀብለዋቸዋል ብሎአል ።

ብፁዕነታቸው ወደ ቤተ መቅደስ ገብተው የሕሊና ጸሎት ካደረሱ በኋላ ታቦተ ሕጉ ወደ ዐውደ ምህረቱ ወጥቶ ሥርዓተ ዑደቱ እንደተከናወነ በተዘጋጀለት ሥፍራ ቆሞ መዘምራኑ ለዕለቱ የሚስማማውን ግሥ በመቃኘት ለ፲፭ ደቂቃ ያህል አሸብሽበዋል ከዚሁ በመቀጠል የሰንበት ት/ቤት መዘምራን ተመሳሳይ መዝሙር አሰምተዋል ። በበዓሉ ላይ የአድባራት አለቆች ሊቃውንትና መዘምራን በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ የአዲስ አበባና ከየክፍላተ ሀገራት የመጡ ምእመናን ተገኝተዋል ።ሲል ሪፖርቱ ያመለክታል

ሐተታውንም በማራዘም የጣዕመ ዝማሬው ስነ ሥርዓት እንዳበቃ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የምዕራብ ጎጃምና የመተከል ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ትምህርትና ምክር ሰጥተዋል ። ካለ በኋላም እያይዞም ብፁዕነታቸው ከሰጡት ትምህርት ስለጻድቁ አባታችን አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተራዳኢነት የቱን ያህል እንደሆነ በስፋትና በጥልቀት አስረድተዋል ቀጥሎም በአዲስ አበባ ምእመናን ትብብር ይህን የመሰለ ቤ/ክርስቲያን ተሠርቶ ለተቀደሰ አገልግሎት መዋሉንና ለዚሁም ሥራ በአሠሪነት ሌት ተቀን እንደተረዳ ቆመው ከፍጻሜ ያደረሱ መልአከ ሕይወት ወልደሰንበት እድሐናና የሰበካ ጉባኤው አባላት በሙሉ በመልካም ሥራቸው ዋጋቸው በመንግሥተ ሰማያት ከፍ ያለ መሆኑን ገልጸው ይህ ሁሉ ለማየት ተሰብስቦ ለመጸለይና የአምልኮታችን ሥነ ሥርዓት ለመፈጸም የቻልነውና የምንችለው በሀገር ነውና ሀገራችን ኢትዮጵያ ሰላሙን እንዲያወርድላት ከልብ መጸለይ እግዚአብሔር አምላካችንን ሌት ተቀን መለመን ይገባናል ሲሉ አባታዊ ምክራቸውን አስተላልፈዋል ።

ከዚህ ቀደም ብሎ ግን መልአከ ሕይወት ወልደ ሰንበት እድሐና ከዚህ የሚከተለውን የወንጌል ትምህርትና ተአምራዊ ሪፖርት ሰጥተዋል አቅርበዋል በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ። ሰላምንና ጤናን የሚሰጥ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጤና ጠብቆ የአባታችን የአቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስን በዓለ ዕረፍት ለማክበር በዚህች



www.ethiopianorthodox.org

ዐውደ ምህረት ለመሰብሰብ እን ኳን አበቃን ካሉ በኋላ አባታችን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዓለም በአካለ ሥጋ ሳሉ በሀገራችን በልዩ ልዩ ሥፍራ ሰልጥነው የነበሩትን አጋንንት እንዳጠፉአቸው ሁሉ ዛሬ ደግሞ በዓፀደ ነፍስ ሆነው በቡል ቡላ ፈለገ ሕይወት ፀበላቸው በልዩ ልዩ ደዌና በአጋንንት ልከፍት የተ ያዙትን በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ወገኖቻችንን እየፈወሱአቸው ነው ይህ አስደናቂ ተአምር አባታችን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዓለም ሳሉ በጾም ፣ በጸሎት ፣ በስግደትና በዕንባ በከፈሉት መንፈሳዊ ተጋ ድሎ ከፈጣሪያቸው በተቀበሉት ቃ ል ኪዳን መሆኑን የማይታበል እው ነት ነው ብለዋል ።

መልአከ ሕይወት ወ/ሰንበት ንግ ግራቸውን በመቀጠል አባታችን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ አንደኛ ሥ ጋቸውን እደንድነው ለሥጋቸው ነጋ ጠባ የሚጨነቁ ሳይሆን የዚ ህን ዓለም ጣዕም የናቁ ለሥጋቸው መሸፈኛ ልብስ የማይፈልጉ ቀን በሐሩር ሌሊት በቊር ወደ ፈጣሪያ ቸው ከመጸለይ አላቋረጡም በጠቅ ላላ ከምግበ ሥጋ የራቁ በመንፈ ሳዊ ጸጋ የረቀቁ በአባትነት የላቁ አባት ናቸው ። እዎን አቡነ ገ/መን ፈስ ቅዱስ ሦስት መቶውንዓመት በግብፅ ፣ በረሀ ፣ ሁለት መቶ ስድሳ ውን ደግሞ በሀገራችን በኢትዮ ጵያ ዱር ገደል ተራራ ሸንተረር በመ ዘዋወር በጾም ፣ በጸሎት በስግደትና በዕንባ በየዋሻውና በየጢሻው እየ ተቀመጡ ስለሀገራችን ብዙ ማል ደዋል አጋንንቱም ጠራርገው አጥ ፍተዋቸዋል ። እኛም የቃል ኪዳን ልጆቻቸው እንድንሆን ጌታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ ቃል ኪዳን ገብቶላ ቸዋል እኛ ዛሬ ይህች በዓል እንዲህ ተሰብስበን የምናከብራት ያለምክ ንያት አይደለም ክቡር አባታችን ያረፉባት ፣ አሥራ ሁለት አክሊ ላት የተቀዳጁበት ስለሆነች በከ ፍተኛ ድምቀት እናከብራታለን ።

ዛሬ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ አባታችን አቡነ ገብ ረ መንፈስ ቅዱስ አባት እንዲሆ ኑን የሰጠን እኛ ደግሞ የአባታችን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ልጆች እን ድንሆን በቃል ኪዳን የተወራረስ ንበት ዕለት ነው ኢትዮጵያውያንን አሥራት አድርጌ ሰጥቸሃለሁ ከማ ለቱም በላይ ስምህን የጠራ በስም ህም የመጸወተ ልጁን በስምህ የሰ የመ ያበላ ያጠጣ በአማላጅነትህ የታመነ እስከ ፵፰ ትውልድ ድረስ ምሬልሃለሁ ብሎ የፈቀደላቸውና ቃል ኪዳን የገባላቸው ዕለት ስለ ሆነች ይህች በዓል ከበዓላት ሁሉ የላቀች ናትና ምእመናን ሁላችሁ ዕልል እንድትሉ ሐሴትና ደስታም እንድታሰሙ ይገባል ሲሉ መል አከ ሕይወት ወ/ሰንበት አድሐና አስተምረዋል ።

በመጨረሻም መልአከ ሕይወት ወ/ሰንበት አድኃና ንግግራቸውን ሲያጠቃልሉ ባሁኑ ጊዜ አባታ ችን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ በቃል ኪዳን የተረከቡአት አገራችን ኢት ዮጵያ ሰላም አጥታ በሁከትና በጦ ርነት ስለምትገኝ የነበረው ሰላምዋ ተመልሶ በፍቅር በአንድነት በሰ ላምና በወንድማማችነት ለመኖር እንድንችል በዚህች ደቂቃና ሰኮ ንድ በተቀደሰው ዐውደ ምሕረት ዙሪያ ተገኝተው ችግራችንን ሁሉ ለመቀበልና ለማቃለል እጃቸውን ወደዘረጉልን አባታችን አቡነ ገ/ መንፈስ ቅዱስ በንጹሕ ልብእናቅ ርብ ፣ ሰላም ጠፍታለች ፍቅር ከመ ካከላችን ጠፍታለች ። ከዚህም የተ ነሣ ሁለት ወንድማማች እየደሙ ባት ትገኛለችና የነበረው ፍቅራ ችንና አንድነታችንን ስመመለስ በሃ ይማኖት ጸንተን ዓይነ ልቦናችንን አንቅተን እንድንማፀን በጥልቅ ኀ ዘን ሆኜ አሳስባችኋለሁ በማለት መ ልአከሕይወት አሳስበው ከጥቅምት ፳ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም እስከ መጋቢት ፳ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም በአባታችን አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ስም በፈ ለቀው ፀበል የተፈወሱትን ሕሙ ማን ዝርዝር መግለጫ ከዚህ እን ደሚከተለው አቅርበዋል ።

፩ኛ/ አቶ ጌታነህ ሙሉነህ ፪ ቀንድ አውጣ ከሆዳቸው የወጣላ ቸው ከአዲስ አበባ

፪ኛ/ አቶ ማርቆስ ፀጋዬ ከአስም በሽታ የዳኑ ከወለጋ ክ/ሀገር

፫ኛ/ አቶ ወሰን ጀንበሬ ፪፻ ልዩ ልዩ አውሬ የወጣላቸ ው ከሀረር ከተማ

፬ኛ/ ፶ አለቃ ተገኘ ከአስም በሽታ የዳኑ ከዲላ ከተማ

፭ኛ/ ወ/ሮ አበበች መርሃ ክርስ ቶስ ፭፻፳፩ ልዩ ልዩ አውሬ የወጣላቸው ከአሰላ ከተማ

፮ኛ/ ወጣት ሲሳይ ወ/ጻድቅ ከመ ታወር (ከአይነ ስውርነት) የዳነ ከአ/አ

፯ኛ/ አቶ ውብሸት ሰይፈ መለ ኮት ፬፻ ትላትል አውሬና ፮ ድብልብል ጠጠር የወጣ ላቸው ከጅማ

፰ኛ/ አቶ ታደሰ ናግራው ፳፩ አባ ጨጓሬ መሰል አውሬ የወጣላቸው ከአዲስ አበባ

፱ኛ/ አቶ ይመር ዮሴፍ ከጉበት በሽታ የዳኑ ከአዲስ አበባ

፲ኛ/ ወ/ሮ እቴነሽ ማኅደረ ማር ያም ከጉበት በሽታ የዳኑ ከኢሉባቦር ክ/ሀገር መቱ

፲፩ኛ/ ወ/ት ዓይናለም ስዩም ከአ ስም በሽታ የዳኑ ከሻሸ መኔ

፲፪ኛ/ አቶ አበሹ ተክሌ ፴፩ ልዩ ልዩ ቀንድ አውጣ የወጣ ላቸው ከሙገር

፲፫ኛ/ ወ/ሮ አበበች ተሊላ አንድ ስ ንዝር የሚያህል አውሬ ፀጉር ለበስ የወጣላቸው ከአ/አ

፲፬/ ወ/ት ትእግስት ፍትዊ ከሸ ባንት የዳነች ከአ/አ

፲፭ኛ/ አቶ ገብሩ ዓለማየሁ ፮፻፴፮ ልዩ ልዩ ትላትል በአንድ ከረጢት የወጣላቸው ከድ ሬዳዋ ከተማ



[illegible] ጸለየ አቡ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በፈለገ ሕይወት ቡልቡላ



www.ethiopianorthodox.org

፲፮ኛ/ ወ/ሮ በላይነሽ የገዛ የእናታቸው ልጅ መድኃኒት ካቀመሰቻቸው በኋላ ፩፪፱ እንቁላል የመሰለ አውሬ የሚሙህየወጣላቸውከአሰብከተማ

፲፯ኛ/ ወ/ት ይርጋለም ሰይድ ፳፩ ፀጉርለበስአውሬየወጣላቸው ከደብረ ብርሃን

፲፰ኛ/ ወጣት ለማልሞ ከስኳር በሽታ የዳነች ከወለጋ ክ/ሀገር ነቀምቴ አውራጃ

፲፱ኛ/ ወ/ት መሰሉ ነጋሽ ከስኳር በሽታ የዳነች ከናዝሬትከተማ

፳ኛ/ አቶ ዓለም ሰገድ መኰሪያ ከአስም በሽታ የዳኑ ከአ/አ

፳፩ኛ/ አቶ ይስማው ወ/ማርያም ፳፩ ዓመት ሙሉ ሽባ የነበሩና የዳኑ ከጎጃም ክ/ሀገር መተከል

፳፪ኛ/ አቶበፍብህ እንያቸው ፬፻፳፬ ልዩ ልዩነፍሳትየወጣላቸው ከአርሲ ክፍለ ሀገር ጭላሎ አውራጃ

፳፫ኛ/ ተማሪ ደምመላሽ ዜናዊ ፲ ዓመት ሙሉ መንቀሳቀስና መቆም መሄድ አቅቶት የነበረ የዳነ ከአምቦ ከተማ

፳፬ኛ/ አቶ ጣሰው ባልቻ ከጉበት በሽታ የዳኑ ከአ/አበባ

፳፭ኛ/ ወ/ሮ ትበርህ አርአያ ፯ ቀንድ አውጣ የወጣላቸው ከአ/አበባ

፳፮ኛ/ አቶ ገ/ጻድቅ መስፍን ከስኳር በሽታ የዳኑ ከጎርደማ እግዚአብሔር አብ

፳፯ኛ/ ወ/ሮ አሰፋ ህሉፍ ፬ አባጨጓሬ መሰል አውሬ የወጣለት ከአሰበ ተፈሪ

፳፰ኛ/ አቶ ዓለማየሁ እንግዳሰው ከአስም በሽታ የዳኑ ከአ/አበባ

፳፱ኛ/ ወ/ት አበባነሽ ጌታሁን ፯ አባጨጓሬ መሰል አውሬ የወጣላትከነገሌ ቦረና አርሲ

፴ኛ/ ወ/ሮ ዘውድነሽ ኪዳነ ማርያም ፳፩ ዓመት ሙሉ በአስም በሽታ ተይዘው የነበሩና የዳኑ ከሲዳሞ ክ/ሀገር ክብረ መንግሥት

፴፩ኛ/ ወ/ሮ እንዘዝሽ ወ/ሚካኤል ፩፻፳፩ ልዩ ልዩ ነፍሳት የወጣላቸው ከአ/አበባ

፴፪ኛ/ አቶ ኪዳነ ማርያም ተስፋዬ አሁንም ከጉበት በሽታ የዳኑ ከአ/አበባ

፴፫ኛ/ ወ/ሮ መስታወት እንያቸው ፳፪፴፩ ልዩ ልዩ አውሬ የወጣላቸው ከአ/አበባ

፴፬ኛ/ አቶ ነሲቡ ፀሐይዬ ከአስም በሽታ የዳኑ ከሲዳሞ ክ/ሀገር አዋሳ ከተማ

፴፭ኛ/ አቶ ቅጣቸው መድኅን ፳፩ ዓመት ሙሉ ሽባ ሆነው የዳኑ ከሀረር ከተማ

፴፮ኛ/ ወ/ት አቦነሽ ፩፻፸፯ ነፍሳት የወጣላቸው ከአ/አበባ

፴፯ኛ/ ተማሪ ተክሉ ብንያም ከሽባነት የዳኑ ከሐረር ከተማ

፴፰ኛ/ ወ/ሮ ወይንሸት መንግሥቱ ፩ አባጨጓሬና ፩ ጊንጥ መሰል አውሬ የወጣላቸው ከአ/አበባ

፴፱ኛ/ ወ/ሮ ከበቡሽ ተስፋሁን ከአስም በሽታ የዳኑ ከአ/አበባ

፵ኛ/ ወ/ሮ ተክኤን ገ/ግዮ መካን የነበሩ በ፴፱ ዓመታቸው የወለዱ ከአሰብ ከተማ

፵፩ኛ/ ከአጋንንት ልክፍት የዳኑ ፩ሺህ፬፻፹

፵፪ኛ/ ጆሮአቸው የሚመግልባቸው ፱፻፴፩

፵፫ኛ/ ልባቸውን የሚታመሙ ፳፻፳፯

፵፬ኛ/ በዛርና በቡዳ የተለከፉ፱ሺ ፳፻፵፱

፵፭ኛ/ ሆዳቸውን የሚያቃጥላቸው አውሬ የወጣላቸው ፩ሺ፳፫

፵፮ኛ/ ከጨጓራ በሽታ የዳኑ ፬፻፳፯

፵፯ኛ/ አብደው የነበሩ ፩ሺ፩፻፹፱

፵፰ኛ/ ከስኳር በሽታ የዳኑ ፵፫

፵፱ኛ/ ከጉበት በሽታ የዳኑ ፳፩

፶ኛ/ ዐይናቸውን በትራኮማ ታውረው የነበሩ ፲፬

ጠቅላላ ድምር ፲፰ሺ፫፻፴፫

በተጨማሪም ይህ በእናንተ አሳሳቢነትና ያላሰለሰ የሌት ተቀን የጉልበት የማቴሪያልና የገንዘብ አስተዋጽኦ ይህንን መስሎ አሸብርቆና ደምቆ የሚታየው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን አሁንም ሥራው ያል ተጠናቀቀ በመሆኑ የእናንተኑ እጅ እንጠብቃለንና አባታችን አቡነ ገ/ መንፈስ ቅዱስ እጃቸውን እንዲዘረጉልን እኛም ወደ እርሳቸው እጃችንን በመዘርጋት የጀመርነውን ለመፈጸም እንድንችል ያለ ንን የአቅማችንን ያህል ርዳታ እጠይቃለሁ በማለት የመጨረሻ ንግግራቸውን ደምድመዋል ።



# የ ሰንበት ት/ቤት ዓምድ

## አዘጋጅ ዲያቆን በላይ ጸጋዬ
## ተተኪ ያስፈልጋል

ለአንድ ነገር የወደፊት ህልውና አስተማማኝ ሊያደርጉ የሚችሉተተኪ የሚሆኑ ነገሮች ያስፈልጋሉ። በቤተ ክርስቲያንም ረዘም ካሉ ዓመታት በፊት ጀምሮ ዛሬ ባሉት የቤተ ክርስቲያን አባቶችና እናቶች እግር የሚተኩ ሕፃናትን ማፍራት እንዲቻል የሰንበት ት/ቤት መቋቋሙ ግልጽ ነው ።

የሰንበት ት/ቤት ዋናው ዓላማ ወጣቶችን በአንድነት አሰባስቦ የእግዚአብሔርን ቃል ለማስጠናትና የወንጌልንም ብርሃን በወጣቶቹ መሃሪያነት ለመላው ወጣቶች አዳርሶ ለመጭው ትውልድ ለማስተላለፍ ነው ። እንዲሁም የቤተ ክርስቲያናችንን ሕግና ሥርዓት መሠረታዊ እምነቷን ጭምር በተብራራና በተሻሻለ መንገድ ለመጪው ለማስተላለፍና ለዘመኑም ወጣቶች ለማሳወቅ ት/ቤቱ እጅግ ጠቃሚ ነው ።

የሰንበት ት/ቤት የተጀመረው በሐዋርያት ነው ይህንንም በሐዋ ሥ. ም. ቍ. ፩፥፳ ያለውን ታሪክ ስንመለከት በሐዋርያት ላይ ክርስቶስ እኒህን ሰባቱን አስተማሪዎች የሚመሯችሁ ሐዋርያት ከእናንተ ውስጥ ምረጡ ስለአሉአቸው መርጠው አቀረቡ እናርሱም ሾሙአቸው ።

ለዚህም መረጃ የሚሆነን የእስጢፋኖስ ታሪክ ነው ። እስጢፋኖስ ሕይወቱን የሰጠው በማስተማር አገልግሎት ስለሆነ በ፪ኛ ደረጃም የፊልጶስን ታሪክ ብንመለከት የኢትዮጵ ያዊውን ጃንደረባ አጥምቆ የላከልን ከእነዚህ ተመራጭ ወጣቶች ውስጥ አንዱ ነው ። እነዚህም ወጣቶች ሰማርያ ሄደው ሲሞንን ያህል መሠርይ አሳምነውና አጥምቀው የመጡ ናቸው ።

በአሁኑ ጊዜም የሰንበት ት/ቤት ዓላማ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየመጡ የሚማሩ ተማሪዎችን በመማር ብቻ እንዲያሳልፉ ሳይሆን አስተማሪዎችም ሆነው እንዲማሩ ለማድረግ ነው ። ይህ ጠቃሚነቱ ብዙ ሲሆን በሰንበት ት/ቤት የሰለጠነች ተማሪ እናት ስትሆን ለልጅዋ አስተማሪ ነች ። በሰንበት ት/ቤት የነበረ ተማሪ ኋላ አባት ሲሆን የልጁ አስተማሪ ነው ። በሰንበት ት/ቤት ያላደጉ ወጣቶች ታማኝነት ይጉድላቸዋል ማለት ለወላጆቻቸውና ለሀገራቸው ባልንጀሮቻቸውና ለፈጣሪያቸው ታማኝነት የተሞላበት አገልግሎት ለመስጠት ብቃት አይኖራቸውም ።

በሰንበት ት/ቤት ያደጉ ወጣቶች ግን ለፈጣሪያቸውና ለወላጆቻቸው ይቅርና ለባልንጀሮቻቸውም ታማኞች ናቸው ።

የዛሬዎቹ ወጣቶች እንዲህ ሁነን ከተገኘን ቤተ ክርስቲያናችን ባለ ብዙ ልጅ ትባላለች ። ለካ እንዲህ ዓይነት ልጆች አሏት እንዲያሰኛት በሰንበት ት/ቤት የሠለጠነ የተጣራ ተማሪ በልዩ ሃይማኖት አይወሰድም (ሮሜ ፣ ፲፮ ፣ ፲፯—፳ ። ቤተ ክርስቲያኑን ሃይማኖቱን የሚያኮራ ደግ ልጅ ይሆናል።

የወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ተገኝቶ ሥነ ምግባርን መማር ሃይማኖትን ማጥናት በዚህ ዓለም ላይ ስንኖር የሚያጋጥሙን ብዙ ጊዜያዊ ችግሮች አሉ ለምሳሌም ማጣት ፣ መታመምና በሥራ አለመደሰት በጠቅላላው በዚህ ዓለም ላይ የመኖር ተስፋ የመነመነ ይሆንብናል ። ተኑም የጨለመ ይመስለናል ። መበሳጨትን ፣ ማዘን መተከዝን እናዘወትራለን ይህ ሁሉ ግን ከችግር በሽታ ሊያድነን አይችልም ። ለምሳሌ አንድ ሰው አጣሁ ተቸገርኩ ብሎ ራሱን ቢያጠፋ ታመምኩ ብሎ እግዚአብሔርን ቢያማርር በእግዚአብሔር ሥልጣን ገብቶ እኔው ፈላጭ ቆራጭ ልሁን ብሎ እንደማሰብ ይቈጠራል ።

እርግጥ በአካባቢያችን ሆኑ በኑሮአችን ሰላምን ትዕግስትን የሚያሰጡ ነገሮች አሉ ። ታዲያ እኮ ያን የመከራ ባሕር የምንሻገረው በሰንበት ት/ቤት ታቅፈን የእግዚአብሔርን ቃል ተምረን በትዕግሥት እግዚአብሔርን በመለመን እንጂ በትግልና በኃይል በመመካት አይደለም ።

እያንዳንዳችን በጽሞና ራሳችን ግን እንደሆን ልንገነዘበው እንችላለን ከዚያም ትዕግሥትን ጓደኛና ገንዘብ እናደርጋለን ማለት አንድ ሰው በትዕግሥት ሁሉን ነገር ካደረገ እንደዚያ እንዳሰማርቆ ይታየው የነበረውን ደረጃ በቀላሉ የማይችልበት ምክንያት የለም እሱ ትምህርት አጥቶ ስለተወራጨ ከሕመሙ ሊፈወስ ከችግሩ ሊድን አይችልም ።

ይህም ብቻ አይደለም በወጣትንትህ ዘመን ፈጣሪህን አስብ እንደተባለው ሁሉ ለእያንዳንዳችን ወጣቶች እግዚአብሔር አምላክ የሥራ ፍሬ የሚፈልግበት ቀን አለማንም ሳይለይ የሥራ ፍሬ መልቀሚያው ጊዜ መምጣቱን ሁላችንንም ልንገነዘበው ይገባናል ምናልባት ቀኑንና ሰዓቱን ለማወቅ ያዳግተን ይሆናል ።



www.ethiopianorthodox.org

ዳሩ ግን ይህንን ሰዓትና ቀን በዋዛና ፈዛዛ እና ሳልፈው ሳንል በሥራ ቀንበር ተጠምደን እንድን ቆይና እንድንጠባበቅ ያስፈልጋል ክርስቶስ በሚመጣበት ወቅት ቁጥ ራቸው የማይገመት ሕዝብ የሥራ ፍሬያቸውን በፍጥነት ያቀርባሉ። የሚራመዱ ። ነገሮች ሁሉ ተቋር ጠው የሥራ ፍሬ ብቻ ይከናወ ናል እያንዳንዱም ሰው በፍርሃት ተውጦ የሚፈረድበት ወይም የሚ ፈረድለትን ለመስማት ይጠብቃል በዚያ በሚያስፈራ ጸጥታ ቀላ ልና ከባድ ሥራ የሠሩ ይገኙባቸ ዋል ። ሁሉም ተሰብስበው ከእ ግዚአብሔር ፊት እየቀረቡ ቃላቸ ውን ይሰጣሉ በዙፋኑ ላይ የተቀመ ጠውን የሥራ ፍሬ ፈላጊ የሆነ ውን ዓይኖቻቸው እንዳያዩ ተራ ሮች እንዲደፋባቸው የሚመኙ አይ ታጡም ። የሥራ ፍሬ ይዘው የቀ ረቡት ግን እግዚአብሔር እውነ ተኛ ፈራጅ መሆኑን ስለሚያውቁ በሥራቸው ይደሰታሉ ።

በዚያ ወቅት ሹመት የጎሳ ልዩ ነት ፣ ሀብት ፣ ዝና ፣ ክብር ትምህ ርትና የቀሩትም በእግዚአብሔር ፊት ምንም ዋጋ የላቸውም ። ዶብ ዳቤ ጽፎ አደራ ስልክ ደውሎ የኔ ነውና ማለት አይኖርም ። በዚያን ጊዜ የሚድኑና ተቀባይነት የሚ ኖራቸው መዋዕለ ዘመናቸውን ሁሉ ከወጣትነታቸው ጀምሮ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ ከቃሉ የተ ማሩ መንፈሳዊ ሕይወትን

ያዘወተሩ ሃይማኖታቸውን

የጠበቁ እነዚህ ብቻ ሞገስን ያገኛሉ ።

ስለዚህ የዛሬዎቹ ወጣቶች የሆን ለመዳን የሚያበቃንን ሥራ መስ ራት እንድንችል በትጋሚያ ራሳ ችንን ለእግዚአብሔር በመስጠት በሰንበት ገ/ቤት ተደራጅተን ከቃ ሉ ለመማር መፈንሳዊ ሕይወትን ይዘን ሃይማኖታችንን ጠብቀንና ረክተን መኖር እንድንችልና በእ ግዚአብሔር ፊት ሞገስ እንድናገኝ ያስፈልጋል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በጥበብና በቁመት በሞገስም በእ ግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነ በር ሉቃስ ፤ ፪ ፤ ፶፪ ይላልና ፪ኛም ወጣቶች በሰው ፊት በቁመት ብቻ ልናድግ ስለማያስፈልግ በእግዚአ ብሔር ፊት በሞገስና በጥበብ እን ድናድግ በሰንበት ት/ቤት እንሰባ ሰብና እንማር ።

www.ethiopianorthodox.org